# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ረቡዕ | 83ኛ ዓመት ቁጥር 219 ሚያዝያ 9 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









ፎቶ፡- በረሁን ታደሰ

# የባህር ወንበዴዎቹ ሲሳዮች

**አዲሱ ገረመው**

የ34 ዓመቱ ኢትዮጵያዊ ከአውሮፕላኑ ሲወርድ እግሮቹ ቆስለው መራመድም ሆነ መቆም አቅተውታል። ብርክ ይዞት ይንገዳገዳል፡፡ ይህ ሰው የተሻለ ህይወት ይኖረናል ብለው በሕገ ወጥ መንገድ ወደ ሳኡዲ ዓረቢያ በባህር ላይ ተጉዘው ለእንግልት ከተዳረጉ ዜጎች መካከል አንዱ ነው፡፡

አብዱረሃማን ከማል ይባላል፡፡ ምስራቅ ሀረርጌ ባበሌ የትውልድ ሥፍራው ናት፡፡ በሱማሊያና በየመን አድርገን ወደ ሳኡዲ ዓረቢያ ለመግባት ሲሞክር አሲር በሚባል የሳኡዲ ቦርደር በኩል ዛራን አልጀኑ በምትባል ከተማ ለእስር ተዳርጓል፡፡

የባህር ወንበዴዎቹ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ዩኒቨርሲቲው ከ350 በላይ ለመድኃኒትነት በሚውሉ እጽዋት ላይ ምርምር እያካሄደ ነው

**በሞገስ ተስፋና ሙሉቀን ታደገ**

ቦንጋ፡- ከባህላዊ ሐኪሞች ጋር በመተባበር ከ350 በላይ በሚሆኑ ለመድኃኒትነት በሚያገለግሉ እጽዋት ላይ ምርምር እያካሄደ መሆኑን የቦንጋ ዩኒቨርሲቲ አስታወቀ፡፡ የእንሰት እርሻን ከኢትዮጵያ በተጨማሪ ወደሌሎች የአፍሪካ ሀገራት ለማስፋፋት እየሠራ ነው፡፡

የቦንጋ ዩኒቨርሲቲ የአካዳሚክ ምርምር ቴክኖሎጂ ሽግግርና የማህብረሰብ አገልግሎት ምክትል ፕሬዚዳንት ከለላው አዲሱ (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ከ350 በላይ እጽዋት ተለይተው በአንድ ማዕከል ውስጥ እንዲበዙና እንዲቀመጡ በማድረግ የምርምር ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛል፡፡

ዩኒቨርሲቲው ቡድን አዋቅሮ በየወረዳው ከሚገኙ የባህላዊ ሐኪሞች ጋር እጽዋትን ለይተው እንዲያሰባስቡና በአንድ ማዕከል ውስጥ እንዲበዙና እንዲቀመጡ ማድረጉን አስረድተዋል።

ዩኒቨርሲቲው ከ350... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



# የኮይሻ ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት የግንባታ ጥራት በጥብቅ ቁጥጥር እየተመራ ይገኛል

**ኢያሱ መሰለ**

ኮይሻ፡- የኮይሻ ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት የግንባታ ጥራት ከግብዓት አቅርቦት እስከ ሥራው ሂደት በጥብቅ ቁጥጥር እየተመራ መሆኑ ተገለጸ፡፡

በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል የኮይሻ ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት የሲቪል ሥራዎች ቡድን መሪ ኢንጂነር እሸቱ ወርቁ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የኮይሻ ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት የግንባታ ጥራት ከግብዓት አቅርቦት እስከ ሥራው ሂደት ድረስ፤ በግንባታው ላይ የየራሳቸው የሥራ ድርሻ

የኮይሻ ኃይል ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ኢትዮጵያን በተለያዩ መስኮች ውጤታማ ለማድረግ የሰው ሠራሽ አስተውሎትን በስፋት መጠቀም ይገባል

## - ኢንስቲትዩቱ "አስተውሎት" የተሰኘ ሳይንሳዊ ፊልም አስመርቋል

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያን በተለያዩ መስኮች ውጤታማና ተወዳዳሪ ለማድረግ የሰው ሰራሽ አስተውሎትን መጠቀም እንደሚገባ የኢትዮጵያ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት አስታወቀ፡፡

ኢንስቲትዩቱ በእውነተኛ ታሪክ ላይ የተመሰረተ “አስተውሎት” የተሰኘ ሳይንሳዊ ፊልም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በተገኙበት ትናንት አስመርቋል፡፡

በምርቃቱ ወቅት የኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ወርቁ ጋቸና (ኢ/ር) እንደገለጹት፤ ሰው ሠራሽ አስተውሎት በርካታ ሀገራት ችግራቸውን የሚፈቱበት ዋነኛውና ቁልፍ መሳሪያ ነው፡፡

ሰው ሠራሽ አስተውሎትን በርካታ ሀገራት በዘርፉ ፈጣን እድገት እያስመዘገቡበትና የመወዳደሪያ አውድ እያደረጉት ነው ያሉት ኢንጂነር ወርቁ፤ ኢትዮጵያም

ኢትዮጵያን በተለያዩ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ - ዳኜ አበራ

ወርቁ ጋቸና (ኢ/ር)




# የኢትዮ-ጅቡቲ ባቡር ትራንስፖርት በዘጠኝ ወራት 2 ነጥብ 84 ቢሊዮን ብር አገኘ

**ፋንታነሽ ክንዴ**




አዲስ አበባ፡- ባለፉት ዘጠኝ ወራት ሁለት ነጥብ 84 ቢሊዮን ብር ገቢ ማግኘቱን የኢትዮ-ጅቡቲ ባቡር ትራንስፖርት አክሲዮን ማህበር አስታወቀ፡፡

በኢትዮ-ጅቡቲ ባቡር ትራንስፖርት አክሲዮን ማህበር ቺፍ ኮርፖሬት ስትራቴጂ ኦፊሰር አቶ አሚኑ ጁሀር ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ አክሲዮን ማህበሩ በበጀት ዓመቱ ከባቡር አገልግሎቶች 3 ነጥብ 7 ቢሊዮን ብር ለመሰብሰብ አቅዶ በዘጠኝ ወራት ውስጥ 2 ነጥብ 84 ቢሊዮን ብር መሰብሰብ ችሏል፡፡

የተገኘው ገቢ ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር የ67 ሚሊዮን ብር ብልጫ እንዳለው አቶ አሚኑ አመላክተዋል።

ማህበሩ በዘጠኝ ወራት ውስጥ መንገደኞችን የማጓጓዝ አቅሙን 155 ሺህ ለማድረስ አቅዶ 148 ሺህ 664 መንገደኞችን ማጓጓዙን ጠቁመው፤ አፈጻጸሙ 95 ነጥብ ዘጠኝ በመቶ መሆኑን ገልጸዋል።

በዘጠኝ ወሩ የተጓጓዘው መንገደኛ ብዛት ባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ከተጓጓዘው ጋር ሲነጻጸር የ19 ሺህ 664 ልዩነት ያለው ሲሆን የ15 በመቶ እድገት አሳይቷል ብለዋል፡፡

በዘጠኝ ወሩ ሁለት ነጥብ 01 ሚሊዮን ቶን የገቢና ወጪ ጭነት ለማጓጓዝ ታቅዶ አንድ ነጥብ 442 ሚሊዮን ቶን ጭነት ማጓጓዝ መቻሉን አመላክተው፤ ይህም የእቅዱን 71 ነጥብ ስድስት በመቶ የሚሸፍን መሆኑን አስረድተዋል። በዘጠኝ ወሩ የተጓጓዘው ጭነት መጠን ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር የሰባት በመቶ ቅናሽ እንዳሳየ ጠቁመዋል።

የባቡር ትራንስፖርት መለዋወጫዎች ላይ ባጋጠሙ ብልሽቶች፣ በጭነት ማንቀሳቀሻ ክሬን መስተጓጎል ምክንያት እንዲሁም በቀይ ባህር ባጋጠመ የጸጥታ ችግር ምክንያት የጭነት መጠን መቀነሱን አንስተው፤ በተጨማሪ በጅቡቲ ወደብ በደረሰ የጎርፍ አደጋ ምክንያት ለተወሰኑ ቀናት ኦፕሬሽን መቋረጡ ለጭነት መጠኑ መቀነስ ምክንያት መሆናቸውን ተናግረዋል።

የደህንነት እና ጸጥታ ችግሮች፣ ስርቆት እና ውድመት፣በሰውና በእንስሳት ላይ የሚደርስ አደጋ እና የኤሌክትሪክ ኃይል መቆራረጥ ባለፉት ዘጠኝ ወራት አክሲዮን ማህበሩ ካጋጠሙት ተግዳሮቶች መካከል መሆናቸውን አስታውሰው፤ ችግሮችን ለመቅረፍ ከሚመለከታቸው ባለድርሻዎች ጋር በቅርበት እየተሠራ መሆኑንም አስታውቀዋል፡፡

የኢትዮ-ጅቡቲ ባቡር ትራንስፖርት አክሲዮን ማህበር የባቡር የመጫንና የማውረድ ቅልጥፍናን ባለፉት ዘጠኝ ወራት በሰባት ነጥብ አምስት በመቶ ለማሻሻል አቅዶ ሲሠራ መቆየቱን አስታውሰው፤ የአገልግሎት ማሻሻያው አፈጻጸም በጥናት ላይ እንደሚገኝና ውጤቱ ሲታወቅ ይፋ እንደሚደረግ አቶ አሚኑ ጨምረው ገልጸዋል።

# ጀርመን ለስምንት ማስተማሪያ ሆስፒታሎች የተለያዩ የሕክምና ቁሳቁሶች ድጋፍ አደረገች

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- የጀርመን መንግሥት በልማት ባንኳ አማካኝነት ለስምንት ከፍተኛ ትምህርት ማስተማሪያ ሆስፒታሎች ሦስት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ዩሮ የሚያወጡ የተለያዩ የሕክምና ቁሳቁሶች ድጋፍ አደረገች።

የኒራስ ጀርመን ባዮ ሜድካል ፕሮጀክት ቡድን መሪ ጌሪት ክሉግ ትናንት ድጋፉ በተደረገበት ወቅት እንደገለጹት፤ ለስምንቱ ማስተማሪያ ሆስፒታሎች የሚከፋፈሉት አይሲዩ አልጋዎች፣ ቬንቲለተሮች፣ ኦክሲጅን ኮንሰንትሬተርስና ሌሎችም የሕክምና መሳሪያዎች ናቸው፡፡

ከሕክምና ድጋፉ በተጨማሪ ለጤና አጠባበቅ ስፔሻሊስት እና ቴክኒሻኖች በሥልጠና መስክ የአቅም ማጎልበት ድጋፍም ይሰጣል ብለዋል።

የተደረገው እገዛ የሆስፒታሎቹን አቅም ለማጎልበትና ለተማሪዎች ተግባር ተኮር ትምህርት ለማቅረብ ያግዛል ያሉት ጌሪት ክሉግ፤ ድጋፉ ከዚህ ቀደም በጀርመንና በኢትዮጵያ መንግሥት መካከል ለሕክምናው ዘርፍ ድጋፍ ለማድረግ የተደረገ 16 ነጥብ 5 ሚሊዮን ዩሮ ስምምነት አካል መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

እንደ ቡድን መሪው ገለጻ፤ የሕክምና መሳሪያዎቹ ኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች ለሕክምና ተማሪዎቻቸው የተግባር ተኮር የክህሎት ስልጠና እንዲሰጡ የሚረዱና የጤና ባለሙያዎች ለህይወት አድን ሥራቸው የሚጠቀሙባቸው ናቸው።

ጀርመን ለኢትዮጵያ በተለያዩ ዘርፎች በሆስፒታሎች ውስጥ ያለውን የሕክምና አገልግሎት አሰጣጥ ለማሻሻል የሚያስችል ድጋፍ እያደረገች መሆኑን የገለጹት ጌሪት ክሉግ፤ በቀጣይም የምታደርገውን ድጋፍ አጠናክራ እንደምትቀጥል አመላክተዋል፡፡

በጤና ሚኒስቴር የሰው ሀብት ልማት ማሻሻያ መሪ ሥራ አስፈጻሚ አሰግድ ሳሙኤል በበኩላቸው፤ በጤናው ዘርፍ ላይ ተግዳሮት እየሆነ ያለው የሕክምና ቁሳቁስ እጥረት ነው፤ ይህንን ለማሟላት እንደሀገር ለሚደረገው ጥረት ድጋፉ ትልቅ አስተዋጽኦ አለው ብለዋል፡፡

ድጋፉ ወደ ሕክምና ተቋማት ሲገባ አሁን ላይ እየተሰጠ ያለውን አገልግሎት የበለጠ ለማጠናከርና ጥራቱን ለመጨመር ትልቅ አቅም ይፈጥራል ያሉት አቶ አሰግድ፤ ከሕክምና መሳሪያው በተጨማሪ ብልሽት ቢያጋጥም ጥገና ለማድረግ የሚያስችሉ መሳሪያዎች አብረው መኖራቸው ድጋፉን ለየት እንደሚያደርገው ገልጸዋል።

ድጋፉ በየሆስፒታሉ የሚገኙ የባዮ ሜዲካል ወርክሾፖችን ለማጠናከርም አቅም እንደሚፈጥር ጠቁመው፤ የሕክምና መሳሪያዎቹ ጊዜውን የሚዋጁ በመሆናቸው በሀገሪቱ አሁን ላይ እየተሰጠ ያለውን የሕክምና አገልግሎት ይበልጥ ለማዘመን እንደሚረዱ ጠቁመዋል፡፡

በትምህርት ሚኒስቴር የመሠረተ ልማትና ግብዓት ዴስክ ኃላፊ ዘውዱ ካሳ እንደተናገሩት፤ ድጋፉ በጤና ተቋማት የሚሰጡ አገልግሎቶችን ለማሻሻል፣ የባለሙያዎችን አቅም ለመገንባትና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የትምህርት ጥራትን ለማሻሻል ሚና ይኖረዋል፡፡

ከሚሰጠው የሕክምና መሳሪያ በተጓዳኝ ከፍተኛ ወጪ ተመድቦ ለባለሙያዎችም ስልጠናዎች እንደሚሰጡ የገለጹት የዴስክ ኃላፊው፤ የተደረገው ድጋፍ በማስተማሪያ ሆስፒታሎች ለጽኑ ሕሙማን ሕክምና ለመስጠት እንደሚያስችል ጠቁመዋል፡፡

እንደ አቶ ዘውዱ ገለጻ፤ የጀርመን መንግሥት ለትምህርት ዘርፉ መሻሻል ለረጅም ጊዜ ድጋፍ ሲያደርግ የቆየ ሲሆን፤ ያሁኑ ድጋፍ ትኩረቱን የሚያደርገው በጤና ተቋማት የሚገኙ የላቦራቶሪ፣ የወርክሾፕ መሳሪያዎችን መጠገን የሚችሉ ሠራተኞችን ማብቃት ላይ ነው፡፡

ድጋፉ የተደረገላቸው ጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል፣ ድል ጮራ ሪፈራል ሆስፒታል፣ አዳማ ሪፈራል ሆስፒታል፣ ደሴ ሪፈራል ሆስፒታል፣ ፈለገ ህይወት ሪፈራል ሆስፒታል፣ ጂማ ዩኒቨርሲቲ ሜዲካል ማዕከል፣ አይደር ሪፈራል ሆስፒታልና አርባ ምንጭ ሪፈራል ሆስፒታሎች መሆናቸው በመርሀ ግብሩ ላይ ተገልጿል።

# ሐረሪዎች ያበረከቱት ቅርስና ዕሴት ድንበር ተሻጋሪ ሀብት ሆኗል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



ፎቶ፡- በረሁን ታደሰ

አዲስ አበባ፡- ሐረሪዎች ያበረከቱት ቅርስና ዕሴት ድንበር ተሻጋሪ ሀብት መሆኑን የባሕልና ስፖርት ሚኒስቴርና የቱሪዝም ሚኒስቴር ገለጹ። በሐረሪ ክልል “ሸዋል ዒድ ለኅብረ ብሔራዊ አንድነታችንና ለቱሪዝም እድገታችን” በሚል መሪ ሃሳብ በዓሉ በተለያዩ ዝግጅቶች እየተከበረ ይገኛል።

በሐረሪዎች ዘንድ በድምቀት የሚከበረው የሸዋል ዒድ ዋዜማ ትናንት በተለያዩ ሥነ-ሥርዓቶች ሲከበር በሥነ-ሥርዓቱ ላይ የተገኙት የባሕልና ስፖርት ሚኒስትር ቀጀላ መርዳሳ፤ ሐረር የዳበረ ዕሴትና ባሕል ባለቤት ነች፤ በተለይ የሸዋል ዒድ በዓል ወጣቱ የኅብረተሰብ ክፍል በነፃነት የሚንቀሳቀስበት ነው ብለዋል።

ሐረሪዎች ፍቅርና አብሮነትን ከቀደምቶቻቸው ተቀብለው ለቀጣዩ ትውልድ በማስተላለፉ በኩል እየተወጡት ያለው ሚና የሚደነቅ ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ ያበረከቱት ቅርስና ዕሴትም ድንበር ተሻጋሪ ሆኗል ሲሉ ገልጸዋል። ክልሉ ለሚያደረገው እንቅስቃሴ የቱሪዝም ሚኒስቴር ያልተቆጠበ ድጋፍ እንደሚያደርግም አረጋግጠዋል።

የቱሪዝም ሚኒስትር ናሲሴ ጫሊ በበኩላቸው፤ ሐረር ትውፊታዊና ዕምነታዊ ባህሎች የሚንፀባረቁባት ከተማ መሆኗን ገልጸው፤ ፍቅርና አብሮነት ባህሉ የሆነው የሐረር ሕዝብ በሸዋል ዒድ ዕለት ደምቆ የሚታይበት እንደሆነ ተናግረዋል።

ሸዋል ዒድ በዩኔስኮ የማይዳሰስ ቅርስ መመዝገቡን አስታውሰው፤ በዓሉ ሁሉም የሚያከብረው መሆኑ ለመመዝገቡ ዋነኛ ምክንያት ነው ብለዋል።

አሁንም ክልሉ ለሚያደርገው እንቅስቃሴ የቱሪዝም ሚኒስቴር ያልተቆጠበ ድጋፍ እንደሚያደርግም አረጋግጠዋል።

የሐረሪ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ኦርዲን በድሪ፤ ሐረር ሁለት ቅርሶችን በዩኔስኮ በማስመዝገብ ከሀገራችን ከተሞች ቀዳሚ ነች፤ ይህም ለቱሪዝሙ ዘርፍ የጎላ ሚና አለው፤ ይህን ታሳቢ በማድረግም እንደ ክልል እድሎችን የማስፋት ሥራ እየተከወነ ነው ብለዋል።

የሐረሪ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ኦርዲን በድሪ ሐረር ሁለት ቅርሶችን በዩኔስኮ በማስመዝገብ ከሀገራችን ከተሞች ቀዳሚ ነች፤ ይህም ለቱሪዝሙ ዘርፍ የጎላ ሚና አለው፤ ይህን ታሳቢ በማድረግም እንደ ክልል እድሎችን የማስፋት ሥራ እየተከወነ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

በተያያዘ የሸዋል ዒድ በዓልን ምክንያት በማድረግ የተዘጋጀ የባህል ዐውደ ርዕይና ፌስቲቫል ትናንት በሐረር ከተማ ተከፍቷል።

በባህል ዐውደ ርዕዩና ፌስቲቫሉ አጎራባች ክልሎች እና የአርጎባ የባህል ቡድን እንዲሁም የባህል አልባሳትና ጌጣጌጥ አምራች ማህበራትና ተቋማት ተሳትፈዋል።

ሸዋል ዒድ በተባበሩት መንግሥታት የትምህርት የሳይንስና የባህል ተቋም ዩኔስኮ ለማስመዝገብ አስተዋጽኦ ላበረከቱ አካላት የእውቅና ሰርተፍኬት የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር አቶ ኦርዲን በድሪ እጅ ተረክበዋል።

# በኢትዮጵያ ለጥላቻ ንግግርና የሀሰተኛ መረጃ መስፋፋት የማህበራዊ ሚዲያዎች ሚና ጉልህ ነው

## - በቪዲዮ ከተሰራጩት የጥላቻ ይዘቶች ቲክቶክ ከፍተኛውን ድርሻ ይዟል

**አዲሱ ገረመው**


**አቶ ዮናታን ተስፋዬ**

አዲስ አበባ፡- በተዘጋጀው ሪፖርት መሠረት ኢትዮጵያ ለጥላቻ ንግግርና የሀሰተኛ መረጃ መስፋፋት የማህበራዊ ሚዲያ ገጾች ሚና ጉልህ እንደሆነ የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለስልጣን አስታወቀ፡፡

በኢትዮጵያ በቪዲዮ ከተሰራጩት የጥላቻ ይዘቶች ቲክቶክ ከፍተኛውን ድርሻ መያዙ ተመላክቷል።

ባለስልጣኑ የማህበራዊ ሚዲያ የጥላቻ ንግግርና ሀሰተኛ መረጃን የተመለከተ ሀገራዊ ሪፖርት ትናንት ይፋ አድርጓል፡፡

የባለስልጣኑ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ዮናታን ተስፋዬ በወቅቱ እንደገለጹት፤ ባለስልጣኑ በአዋጅ የተሰጠውን መብት በመጠቀም ባለፉት ስድስት ወራት የማህበራዊ ሚዲያ የጥላቻ ንግግርና ሀሰተኛ መረጃን የተመለከተ ሪፖርት አዘጋጅቷል።

በሪፖርቱ ግኝት መሠረት ለጥላቻ ንግግርና ሀሰተኛ መረጃ ስርጭት የማህበራዊ ሚዲያ ገጾች ለችግሩ መስፋፋት ጉልህ ሚና እንደነበራቸው ተመላክቷል ሲሉ አረጋግጠዋል።

ድርጅቶቹ የተጠቃሚ ማህበረሰቡን ደንብና መመሪያ ቢያዘጋጁም ባስቀመጡት ደንብ መሠረት ችግሩን ለመቀነስ ኃላፊነታቸውን በአግባቡ አልተወጡም ሲሉ ጠቁመዋል።

የማህበራዊ ሚዲያ አገልግሎት አቅራቢ ድርጅቶች የሚሰራጩ መልዕክቶች የኢትዮጵያዊያንን ማህበራዊ ትስስር ተጠቃሚዎችን ቋንቋና ባህል ባገናዘበ መልኩ መሆኑን ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል ብለዋል፡፡ ለዚህም አገልግሎታቸውን በሀገር ውስጥ ቋንቋዎች ማቅረብ እንዳለባቸው አመላክተዋል።

ከአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ጋር በቅርበት ለመሥራትና ጥላቻ ንግግርንና ሀሰተኛ መረጃን ለመከላከል ሪፖርትን መነሻ ያደረጉ ሥራዎች እየተሠሩ እንዳለ ጠቅሰዋል፡፡

ሪፖርቱ የማህበራዊ ሚዲያዎች ምን ያህል በኃላፊነት ሲሰሩ ነበር የሚለውን ለሕዝብ ከማቅረብ ባሻገር የሚነሱ ምክረ ሃሳቦች ለፖሊሲ አውጪዎች ግብአት ሆነው እንደሚያገለግሉ ገልጸዋል፡፡

በባለስልጣኑ የመገናኛ ብዙኃን አቅም ግንባታ ዴስክ ኃላፊ ወይዘሮ ኤደን አማረ ሪፖርቱን ባቀረቡበት ወቅት እንዳመለከቱት፣ በጥላቻ ንግግርና በሀሰተኛ መረጃ ስርጭት ዙሪያ እያንዳንዳቸው የማህበራዊ ሚዲያ አገልግሎት አቅራቢ ድርጅቶች ባወጡት አሠራር መሠረት የማህበረሰብ ደንብና መመሪያ አክብረው ኃላፊነታቸውንና ግዴታቸውን ሊወጡ ይገባል።

ባለፉት ስድስት ወራት በተለያዩ ማህበራዊ ሚዲያዎች በፍረጃ፣ ሰብዓዊነትን በማዋረድ፣ በጭካኔ አገላለጽ፣ ጽንፍ በያዘ አገላለጽና የጋራ እሳቤዎችን በሚንድ መልኩ የጥላቻ ንግግሮች መተላለፋቸውን ኃላፊዋ አመላክተዋል።

እንደ ዴስክ ኃላፊዋ ገለጻ፤ በስድስት ወራት የጥላቻ ንግግር ይዘቶች የተላለፉበት ቅርጽ በዋናነት በጽሑፍ ሲሆን፣ ተጠቃሚዎች በኤክስ (ትዊተር) ማህበራዊ ድረ-ገጽ 66 በመቶ፣ በፌስቡክ 63 በመቶ እና በቴሌግራም 59 በመቶ በስፋት ተጠቅመዋል። በቪዲዮ የተሰራጩ የጥላቻ ይዘቶች በቲክቶክ 74 በመቶ እና በዩቲዩብ 70 በመቶ ሆነው ታይተዋል።

የተሰራጩት የጥላቻ መልዕክቶች ለአመጽና ለጥቃት የማነሳሳት፣ የግለሰብን ሰብእና የመጉዳት፣ የማህበረሰብን ባህልና ወግ በመናድ የሕዝብን አብሮ የመኖር እሴት መሸርሸርን የሚያስከትሉ ሆነው መታያታቸውን ተናግረዋል።

አገልግሎት አቅራቢ ድርጅቶች የኢትዮጵያውያን የማህበራዊ ትስስር ተጠቃሚዎችን ቋንቋ፣ ባህልና እሴት ተረድተው የሚሰራጩ መልዕክቶችን ተከታትሎ የሚያርም ባለሙያ ማካተት እንዳለባቸውም ጠቁመዋል። የማህበራዊ ትስስር ገጽ አጠቃቀምን አስመልክቶ መሠረታዊ ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራ መስራት እንደሚጠበቅባቸውም አመላክተዋል።

የጥላቻ ንግግርና ሀሰተኛ መረጃ እያስከተለ ካለው አደጋ ሰፊና ውስብስብ እየሆነ ከመምጣቱ አንጻር በጉዳዩ ላይ ቀጥተኛ ሚና ያላቸውን ማህበራዊ ትስስር አውታሮች፣ መገናኛ ብዙኃን፣ አዋጁን ለማስፈጸም ሚና የተሰጣቸው መንግሥታዊ አካላት፣ የሲቪል ማህበራትና ኅብረተሰቡ የሚጠበቅባቸውን ሚና እንዲወጡ አሳስበዋል።



# “የዳታ ማዕከሉ እውቅና ማግኘት የሀገሪቱን ኢንቨስትመንት የመሳብ አቅም ያሳድጋል”

**- ይሽሩን ዓለማየሁ (ዶ/ር) የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር ዴኤታ**

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- የዊንጉ አፍሪካ ዳታ ማዕከል ዓለም አቀፍ እውቅና ማግኘቱ የሀገሪቱን ኢንቨስትመንት የመሳብ አቅም እንደሚያሳድግ በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የአይሲቲና ዲጂታል ኢኮኖሚ ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ይሽሩን ዓለማየሁ (ዶ/ር) ገለጹ፡፡

ዊንጉ አፍሪካ ዳታ ማዕከል፤ከአፕ ታይም ዓለም አቀፍ ካምፓኒ የጥራት እውቅና ማግኘቱን አስመልክቶ በትናንትናው እለት መግለጫ ሰጥቷል፡፡

ይሽሩን ዓለማየሁ (ዶ/ር) በወቅቱ እንደገለጹት፤ የዳታ ማዕከሉ እውቅና ማግኘት የሀገሪቱን ኢንቨስትመንት የመሳብ አቅም ከፍ ያደርጋል፡፡

ኢትዮጵያ የዲጂታል ለውጥ ጉዞ እንደመጀመሯ የዳታ ማዕከል ወሳኝ ነገር ነው፡፡ የማዕከሉ መረጃ ደህንነቱ ከ99 ነጥብ 9 በመቶ በላይ የተጠበቀ ነው በሚሉ መስፈርቶች ዕውቅና መሰጠቱ እንደሀገርም ጠቀሜታው ብዙ ነው ሲሉ አስረድተዋል፡፡

ዕውቅናው የዳታ ማዕከሉን መጠቀም የሚፈልጉ ዓለም አቀፍ ኢንቨስተሮች ወደ ሀገሪቱ እንዲመጡ ያግዛል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ከዚህ ጋር ተያይዞ የሥራ እድል ለመፍጠርና ተጨማሪ የቴክኖሎጂ አቅም ለመፍጠር እንደሚያግዝ አመላክተዋል።

በተጨማሪም የእውቀት ሽግግር እንዲኖር፣ ከሀገር ውጭ ዳታ ማስቀመጥ እንዲቀር እና የቀጣናዊ ትስስር እንዲጠናከር ያደርጋል ብለዋል፡፡ መንግሥት ከጉዳዩ ጋር ተያይዞ ድጋፍ ይደረጋል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ቴክኖሎጂው በአፍሪካ ከሦስት ባልበለጡ ሀገራት መኖሩን የተናገሩት ዶክተር ይሽሩን፤ በምሥራቅ አፍሪካ በኢትዮጵያ በዊንጉ አፍሪካ አማካኝነት የተገነባው ማዕከል በዓለም አቀፍ ደረጃ ዕውቅና ማግኘቱ በዘርፉ ትልቅ ስኬት ነው ብለዋል፡፡

የዳታ ማዕከሎችን ለመገንባት መንግሥት ኢንቨስት የሚያደርግ ቢሆንም ሁሉንም አገልግሎቶች በአንድ ጊዜ ማሟላት ስለማይችል እንደ ዊንጎ አይነት ድርጅቶች መጥተው እንዲያለሙ ይጋብዛል፤ ይህም የዲጅታል ትራንስፖርሜሽን ጉዞን ያፋጥናል ሲሉ አስረድተዋል።

ሚኒስትር ዴታው እንደተናገሩት፤ ድርጅቱ በኢትዮጵያ የዳታ ማዕከል ገንብቶ ከአንድ ዓመት በላይ አገልግሎት እየሰጠ ነው፤ የተገኘው ማረጋገጫም ተጨማሪ ሥራዎችን በዘርፉ ለማከናወን ይረዳል።

አፕታይም ካምፓኒ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለዳታ ሴንተሮች ግምገማ የሚያካሄድና የተቀመጠውን መስፈርት አሟልተው ለተገኙ የዳታ ማዕከሎች ልክ እንደ አይ. ኤስ. ኦ እውቅና ይሰጣል ሲሉ አስረድተዋል፡፡

በሌላ በኩል የግል ዳታ ጥበቃ አዋጅ መውጣቱ በቴክኖሎጂ ዘርፍ የሚሰማሩ ባለሀብቶች እና ሥራ ፈጣሪዎችን እንደሚያበረታታ ተናግረዋል፡፡

የዊንጉ አፍሪካ የመንግሥትና ሕግ ጉዳዮች ከፍተኛ ዳይሬክተር አቶ ተሾመ ወርቁ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ ከዳታ ማዕከሉ ጋር የተለያዩ ባንኮች በጋራ እየሠሩ ይገኛል፡፡

አቶ ተሾመ እንደተናገሩት፤ መንግሥት ለኢንቨስትመንት እድል ሲሰጥ የሥራ እድል ፈጠራ አንዱ መስፈርት ነው፤ ዳታ ሴንተሩ ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ ለበርካታ ዜጎች የሥራ እድል ይፈጥራል፡፡

በተሠሩ ጥናቶች መንግሥት ዲጂታል 2025 ጉዞን መጀመሩ እና ኢትዮጵያ ከአፍሪካ በሕዝብ ብዛት ከፍተኛ መሆኗ ሥራውን ለመጀመር ተመራጭ አድርጎታል ብለዋል፡፡

# ዓለም አቀፉ የዩኒቨርሲቲዎች ትብብር ፋይዳው እስከምን?

**አመለወርቅ ከበደ**

**ዜና ትንታኔ**

በዓለማችን የሚገኙ ሀገራት በጤና፣ በኢኮኖሚና በተለያዩ መስኮች ግንኙነት አድርገው ለጋራ ጥቅም እየሰሩ ይገኛል። ተቋማት እርስ በእርስ በሚኖራቸው ግንኙነት ባለሙያ በመለዋወጥና የገንዘብ ድጋፍ በማድረግ ችግሮቻቸውን በጋራ ይፈታሉ።

በዚህ የወዳጅነት ልምድ ደግሞ በርካታ ዩኒቨርሲቲዎች ግኙኝነታቸውን አጠናክረው ተጠቃሚ መሆን ችለዋል። ባለንበት ዘመን ደግሞ ዘመናዊነት እየተስፋፋ የትብብር መስኩም በአካልና በበይነ መረብ አማካኝነት ተጠናክሯል። ያደጉት ሀገራትም የተለያዩ የቴክኖሎጂ ፍሬዎችን ተጠቅመው የትምህርት ዘርፉን እያሳደጉት ይገኛል፡፡

በኢትዮጵያ የሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎችም ከተለያዩ የዓለም ሀገራት ዩኒቨርሲቲዎች ጋር ወዳጅነት ፈጥረዋል፡ ፡ ትምህርት ሚኒስቴርም ቀደም ካሉት ዓመታት ጀምሮ ትብብሩን ለማጠናከር እንደ አንድ ዘርፍ ተይዞ እየተሰራበት ነው፡፡

የዩኒቨርሲቲዎች ወዳጅነት ለትምህርት ዘርፍ እድገት ምን አይነት ፋይዳ ይኖረዋል? በሚሉ ጉዳዮች ዙሪያ የዘርፉ ምሁራን ሃሳባቸውን ሰጥተዋል።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በሥነ-ትምህርተ ኮሌጅ ተመራማሪና መምህር ካሳ ሚካኤል (ዶ/ር) እንደሚልጹት፤ በሀገር ውስጥ አንድ ዩኒቨርሲቲ የ መማር ማስተማር፣ ምርምርና የማህበረሰብ አገልግሎትን የማቅረብ ኃላፊነት አለበት፡፡

ዩኒቨርሲቲዎች አድማሳቸውን በማስፋት ከዓለም አቀፍ ማህበረሰብ ጋር የልምድ ልውውጥ ማድረግ የሚችልበት አማራጭ ሰፊ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡ አንድ ሀገር በሁሉም የዕውቀት ዘርፍ የተሟላ ልምድ ላይኖራት ይችላል፤ በመሆኑም ዩኒቨርሲቲዎች በጋራ መሥራታቸው ወሳኝነት አለው ይላሉ።

ዩኒቨርሲቲዎች በዓለም አቀፍና በሀገር ደረጃ በጋራ መስራታቸው ጋር ያለውን ባለሙያ ሌላው የሚጠቀምበት አንዱ የሠራውን የምርምር ውጤት በጋራ ለመጠቀም ዕድል የሚፈጥር መሆኑን ያስረዳሉ።

ዶክተር ካሳ እንደሚገልጹት፤ ግንኙነቱ እየጠነከረ ሲመጣ ሁለት ተቋማትን ማዕከል ያደረገ የትምህርት ፕሮግራም እንዲቀረጽ እና የጋራ ዲግሪ መስጠት እስከሚቻልበት ሂደት በትብብር መሥራት ይቻላል።

ኢትዮጵያ በተለያዩ ዘርፎች የባለሙያዎች ውስንነት ስላለባት ከሌሎች ሀገራት ዩኒቨርሲቲዎች የምትማረው ነገር ብዙ ይኖታራል ሲሉ ያመላክታሉ፡፡

ከዓለም ሀገራት ዩኒቨርሲቲዎች ጋር የሚደረግ ወዳጅነት እንደ አጠቃላይ በትምህርት ዘርፉ ያለውን ክፍተት ለመሙላት እንደ ኢትዮጵያ ላሉ ሀገራት አስፈላጊ ቢቻ ሳይሆን አስገዳጅም ጭምር ነው ይላሉ፡፡

ተመራማሪው በትብብር መስራቱ ባለሙያዎችን ለመቀያየር፣ ለማሰልጠንና አቅምን ለማጎልበት ያግዛል ሲሉ ያመላክታሉ።

በሀገሪቱ የዩኒቨርሲቲዎች ኅብረት መኖሩን በመጥቀስ፤ በተናጠል ከሚደረገው ግንኙነት ይልቅ በጋራ መወያየትና ከዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር በትብብር መሥራት ከተቻለ እንደሀገር የሚኖረው ጥቅም ከፍ ይላል ባይ ናቸው።

በቀጣይ የኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲዎች በዓለም አቀፍ ደረጃ በጋራ የመሥራት አቅማቸውን ለማሳደግ፤ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በታገዘ መንገድ ከኤምባሲዎች ጋር ግንኙነት በመፍጠር የዩኒቨርሲቲ ለዩኒቨርሲቲ ትብብሮችን ማሳደግ ተገቢ መሆኑን ይጠቁማሉ፡፡

ተመራማሪው እንደሚሉት፤ የተጀመሩ ትብብሮች እንዳይቋረጡ በጋራ ከመንግሥት ብቻ ሳይሆን፤ በዩኒቨርሲቲዎች የሚገኙ ተመራማሪዎችና ምሁራን የራሳቸውን አስተዋጽኦ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

የዩኒቨርሲቲዎች ትብብር ከረጅም ጊዜያት ጀምሮ የነበረ ቢሆንም አሁን ላይ በዲፕሎማሲ ግንኙነት ደረጃ ተይዞ እየተሰራበት ይገኛል፤ አሁን ሥራው ጅማሮ እንደመሆኑ በቀጣይ እየተጠናከረ ይሄዳል የሚል እምነት አለኝ ይላሉ።

በኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ የትምህርት አመራርና አስተዳደር መምህር አማኑኤል ኤሮሞ (ዶ/ር) በበኩላቸው እንደሚገልጹት፤ በዓለም ደረጃ የዩኒቨርሲቲዎች ተወዳዳሪና መልካም ስነ-ምግባር ያለው ዜጋ የማፍራት ተልዕኮ አላቸው፡፡

ዕውቀት ዓለም አቀፋዊ ነው የሚሉት የትምህርት ምሁሩ፤ በዓለም ያደጉና ያላደጉ ሀገራት እንደመኖራቸው የዩኒቨርሲቲዎች ወዳጅነት በጣም ጠቃሚ ነው ሲሉ ይገልጻሉ።

ያደጉ ሀገራት ዩኒቨርሲቲዎች በቴክኖሎጂ አቅማቸው፣ በማህበረሰብ አገልግሎት፣ በፈጠራ ሥራዎችና በእውቀት ደረጃ ከፍተኛ ደረጃ ደርሰዋል። ያላደጉ ሀገራት ዩኒቨርሲቲዎች ደግሞ ካደጉ ሀገራት ተቋማት ጋር በመስራታቸው ሰፊ ልምድ እንደሚገኝ ያስረዳሉ፡፡

በትብብሩ የትምህርት ዕድል የማግኘት፣ የልምድ ልውውጥ ማካሄድ፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር ማድረግ እና ስራቸውን በማስተዋወቅ የሚያድግበትን መንገድ የማመቻቸት ዕድል ይፈጠራል ይላሉ።

እንደ ዶክተር አማኑኤል አገላለጽ፤ ዘመኑ የግሎባላይዜሽን እንደመሆኑ አንዱ ያለውን የምርምር ውጤትና ቴክኖሎጂ በጋራ ለመጠቀም በትብብር መስራት ወሳኝ ነው፡፡

በኢትዮጵያ የሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች ወደራስ ገዝነት እየተሸጋገሩ መሆኑን አንስተው፤ ራስ ገዝ ሆነው ከዓለም አቀፍ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር መወዳጀታቸው የጋራ ተጠቃሚነታቸው ላይ ውሳኔ በመስጠት ተጠቃሚነታቸውን ለማሳደግ እንደሚረዳ ይገልጻሉ፡፡

ዩኒቨርሲቲዎች እራስ ገዝ በሚሆኑበት ወቅትም ከግንኙነቱ ጋር ተያይዞ ምን ምን ማሟላት እንዳለባቸው ግፊት ሊደረግ ይገባል ያሉት ዶክተር አማኑኤል፤ በዚህ ረገድ የትምህርት ሚኒስቴር ወሳኝ ሚና አለው ይላሉ፡፡

ዶክተር አማኑኤል እንደሚናገሩት፤ በሀገሪቱ የሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች በዕውቀትን የመምራት ችግራቸውን ቀርፈውና ሀገር በቀል ዕውቀትን በማሳደግ ትብብራቸውን ማጠናከር ይገባቸዋል።

መምህራኑ እንደሚገልጹት፤ ዩኒቨርሲቲዎች በሌላው ዓለም ከሚገኙ አቻዎቻቸው ጋር የሚፈጥሩት ትብብር ለተማሪዎቻቸው፣ ለተመራማሪዎችና ለሀገር የሚበጅ ትሩፋትን ይዞ የሚመጣ በመሆኑ አቀማቸውን ለማሳደግ ሊጠቀሙበት ይገባል።

# የባህር ወንበዴዎቹ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

አብዱረሃማንና ጓደኞቹ በባህር አቋርጠው ወደ ሳኡዲ ሲጓዙ ነበር የተያዙት። በእስር ቤቱ ያለ ብርድ ልብስና ያለ ሕክምና፤ ንጽህናቸውም ሳይጠበቅላቸው ከፍተኛ በሆነ የምግብ እጥረት፤ በቀን አንድ ጊዜ ብቻ ከሁለት ጉርሻ የማታልፍ ቂጣ እየበሉ በስቃይና በእንግልት 14 ወራትን ማሳለፋቸውን ይናገራል፡፡

የሳኡዲው የስደት ጉዞ ስቃይና መከራ የበዛበት መሆኑን የሚናገረው አብዱረሃማን፤ በእስር ቤት እርስ በእርስ የሚጣሉ እንዳሉ፤ ዝርፊያም መኖሩን፤ ሰብዓዊ መብት የሚባል ነገር ይናፍቃቸው እንደነበር ይገልጻል፡፡ "የዓለም ስቃይ ያለበት ቦታ ነው" ይላል የነበረበትን የእስር ቤት ህይወት "ከገሀነም እሳት" ጋር እያመሳሰለ፡፡

አብዱረሃማን እንደሚለው፤ የባህር ላይ ወንበዴዎች ስደተኞችን በጫካ ውስጥ ስቃይ ያደርሱባቸዋል፡፡ ይህም በርካቶችን ለስነልቦና ጉዳት ዳርጓል፡፡ በሀገሪቷ ከፍተኛ ሙቀት አለ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ለቅጣት ሲባል ከመጠን ያለፈ ቅዝቃዜ ውስጥ ያስቀምጧቸዋል፡፡ ሴቶች የንጽሕና አገልግሎት አያገኙም፡፡ ልብስ ለመቀየር ይቸገራሉ፡፡ ጉልበቱ ሻል ያለው መሳሪያ ይገዛና ከወንበዴዎች ጋር ተሻርኮ ጫካ ይገባል፡፡ ዜጎችን ያገቱ በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ይጠይቃሉ፡፡ ይህ በየዕለቱ ከሚደረገው ቅሚያ ባሻገር የሚፈጸም ድርጊት ነው ይላል፡፡

"በባህር ላይ ወንበዴዎች የተቀጠቀጥኩበት ዱላ ከአንድ ወር በላይ አሳምሞኛል" የሚለው አብዱረሃማን፤ በታሰረበት ወቅት ጀርባው ላይ ቃጠሎ እንደደረሰበት ይናገራል፡፡ አሁን ላይ እግሮቹ እንደ ልቡ እንደማይራመዱለትና በደረሰበት ከፍተኛ ድብደባ ምክንያት እስከ አዕምሮ ጤና ምርመራ እንደሚያስፈልገው ይገልጻል፡፡

"ልክ እንደ አካል ጤና ጉዳት ብዙዎች የአዕምሮ ጤና እክል ገጥሟቸዋል፡፡ ሥራ ከመፈለጉና እንጀራ ከማግኘቱ ይልቅ ጤንነት ይቀድማል፡፡ ሁሉም ነገር የሚገኘው ጤና ሲኖር ነው" በማለት፤ ለተመላሽ ስደተኞች ቅድሚያ ሕክምና እንዲሰጣቸው ይጠይቃል፡፡

"በዚህ መንገድ ለስድስት ጊዜ ያህል ተመላልሻለሁ፡፡ ከሰርኩ እንጂ የተጠቀምኩት ነገር የለም" ሲል አብዱረሃማን ይናገራል፡፡ ዜጎችን ባልተገባ መንገድ የሚያመላልሱ አካላት የባንክ ቁጥራቸው ጭምር ስለሚታወቅ መንግሥት ይህንን አፋላልጎ ደላሎች ላይ ክትትል ማድረግ እንዳለበትም ይመክራል፡፡

አብዱረሃማን እንደሚገልጸው፤ ወጣቱ ወደ ስደት ሄዶ የተሻለ ሥራ እንደሚሰራ ተነግሮት እየተታለለ ለአንድ ጊዜ ጉዞ እስከ 150 ሺህ ብር ለደላላ እያወጣ ነው፡፡ በዚህ ሀገር ውስጥ መስራት ሲቻል የሀገር ሀብትና የወጣት ጉልበት እየባከነ ነው፡፡

ፈጣሪ ለሀገሩ ስላበቀው ከፍተኛ ደስታ እንደተሰማው፤ መንግሥት በችግር ውስጥ ላሉ ወገኖች መድረሱ ትልቅ ሥራ መሆኑንና ዳግም ከዚህ ሀገር ለመውጣት እንደማያስብ ይናገራል።

"ከሚደርሰው ስቃይና እንግልት አኳያ እንጀራ ፍለጋ ሕጋዊነትን የተከተለ መሆን እንዳለበት እመክራለሁ፡፡ ማህበራዊ ኑሮ እንዲጎብትም መላው ሕዝብ ትብብር ማድረግ አለበት፡፡ ሕገ ወጥ ደላሎች የሂሳብ እንቅስቃሴያቸውን ተከትሎ እርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል" ይላል፡፡

የደቡብ ወሎ ዞን ለጋምቦ ወረዳ ነዋሪ የሆነው ወጣት መካሻ አረጋ፤ በ2014 ዓ.ም የ12ኛ ክፍል ተፈትኖ ውጤት አልመጣ ሲለው ስደትን እንደመረጠ ይናገራል፡፡ ከ200 ሺህ ብር በላይ ለሕገ ወጥ ደላላ በመክፈል በባህር ላይ አድርጎ ሳኡዲ ገብቶ ለመሥራት ቢሞክርም ሳይሆንለት ቀረ፡፡ እሱም እንደ ሌሎች ስደተኞች የእንግልትን ጽዋ ሳይጎነጭ አልቀረም፡፡ በሳኡዲ እስር ቤት ከዓመት በላይ ታስሯል፡፡

ለዚህ ሁኔታ ያበቃው የጓደኛ ግፊት መሆኑን የሚናገረው መካሻ፤ "የስደትን ጉዳት ባለማየት የወሰነው ውሳኔ ትልቅ ዋጋን እንዳስከፈለው ይጠቅሳል፡፡ "በስደት የገጠመን ከሚወራው ነገር ፍጹም የራቀ ነው፡፡ ስቃይና እንግልት የበዛበት ነው፡፡ ከብዙ ወንበዴዎች ሽሽት ብዙ መከራ ደርሶብኛል፡፡ ድንበር ላይ የሞቱ ብዙዎችን አይቻለሁ፡፡ አብሬያቸው ከሄድኩት ዘጠና ወጣቶች ነን የተረፈነው በጣም ጥቂቶች ነን ይላል፡፡

"ስደት አስከፊ ነው ለጠላቴም አልመክርም፤ ለችግሩ የሚዳርገው ደግሞ አለማስተዋል ነው"በማለት፤ ወጣቶች ከስደት ይልቅ በሀገራቸው ተፍጨርጭረው ሰርተው መለወጥ እንዳለባቸው ይመክራል፡፡

"በእሬሳ ላይ እየተራመድን ነው የምንሄደው፡፡ እስር ቤቱም ቢሆን ብዙ በሰቀቀን የተሞላ ነው፡፡ በአንድ ልብስ ዓመት ሙሉ እንቆያለን፡፡ በሽታ ይዞን የሚለቀን ታክምን ሳይሆን በራሱ ጊዜ ነው" ይላል የስደትን አስከፊነት ሲገልጽ፡፡ ከዚህ በኋላ ማንኛውንም አይነት ሥራ ቢሆን ሳይንቅ ለመሥራት ዝግጁ መሆኑንም ነው የሚናገረው፡፡

መንግሥት በጠንካራ የክትትል ሥራዎች በርካቶችን ከአስቸጋሪ ሁኔታ ወደ ሀገራቸው እንዲገቡ እያደረገ ላለው በጎ ተግባርም መካሻ ምስጋናውን አቅርቧል፡፡

የሦስት ዓመት ልጅ እና የሰባት ወር ልጅ ይዛ ወደ ሀገራቸው የተመለሱት ወይዘሮ ነሂማ አህመድ በበኩላቸው፤ ሰርቼ እለወጣለሁ በማለት ልጅ ይዘው ወደ ስደት ቢሄዱም እንዳልተሳካላቸው ይገልጻሉ፡፡ እንጀራ ፍለጋ ወጥተው ገንዘባቸው ለባህር ላይ ወንበዴዎች ሲሳይ ሆኖ ቀርቷል፡፡ ለ10 ወራት ያህል ከልጆቻቸው ጋር የእስር ቤትን ስቃይ ቀምሰዋል፡፡ በስደት ቆይታቸው ልጅ ይዞ እስር ቤት መግባት አስቸጋሪው የህይወት ፈተና እንደነበር ጠቅሰው፤ ሁሉም ሰው በእንዲህ መንገድ ለስደት መዳረግን ምርጫው ማድረግ እንደሌለበትም ይመክራሉ፡፡

ምንም እንኳን አስቸጋሪው የህይወት ውጣ ወረድ ትልቅ ጠባሳ ጥሎባቸው ቢያልፍም ከነ ሙሉ አካላቸውና ከነ ልጆቻቸው ለሀገራቸው ለመብቃታቸው ለመንግሥት ምስጋናቸውን አቅርበዋል፡፡

# የኮይሻ ኃይል...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ባላቸው ሦስቱም ባለድርሻ አካላት በጥብቅ ክትትልና ቁጥጥር እየተመራ ነው፡፡

በሥራ ተቋራጩ "ዊ ቢውለድ"፣ በሥራው ባለቤት የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይልና በአማካሪው "ስታንቴክ" በኩል የግንባታው የጥራት ደረጃ በተቀመጠው መመዘኛ መሠረት መሠራቱን የመከታተል፣ የመቆጣጠርና የማረጋገጥ ሥራ በመናበብ ይሠራል ብለዋል፡፡

ሦስቱም ባለድርሻ አካላት የግድቡን የጥራት ደረጃ ከማረጋገጥ አንጻር እንደ ተሰጣቸው ኃላፊነት 24 ሰዓት ጥብቅ ክትትል ያደርጋሉ ሲሉ አስረድተዋል፡፡

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል በይበልጥም የግንባታውን የጥራት ደረጃ የማረጋገጥ ኃላፊነት እንዳለው የተናገሩት ኢንጂነር እሸቱ፤ የግድቡን ሙሌትና የኃይል ማመንጫ ግንባታ 24 ሰዓት እየተከታተለ በጥራት ደረጃው ዝርዝር ላይ በተቀመጠው መሠረት ስለመከናወኑ እያረጋገጠ መሆኑን አስረድተዋል።

የድርጅቱ የጥራት ደረጃ ተቆጣጣሪዎች ችግር አለበት ብለው ያመኑበት ነገር ቢኖር እንኳን ከሚመለከታቸው አመራሮች ጋር በመነጋገር አፋጣኝ መፍትሔ እንዲሰጥ ያደርጋሉ ብለዋል፡፡

የጥራት ደረጃን የማረጋገጥ ሥራው ከግንባታው አስቀድሞ በነበረው የቦታ መረጣ እንዲሁም ግድቡን ከሚሸከመው የመሬት አቅም ጀምሮ እንደተረጋገጠ አስታውሰው፤ የኮይሻ ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት የጥራት ደረጃ እስከ ግድቡ መጠናቀቅ ድረስ በሦስቱም ባለድርሻ አካላት ትብብር ፣ ጠንካራ ክትትልና ቁጥጥር እየተደረገበት የሚቀጥል መሆኑን ኢንጂነር እሸቱ አስረድተዋል።

የተቋራጩ "ዊ ቢውልድ" የጥራት ተቆጣጣሪ ሙያተኛ ኢንጂነር ፍቃዱ ቸኮል በበኩላቸው፤ ለግድቡ ሥራ ብቻ እርሳቸውን ጨምሮ 11 የጥራት ተቆጣጣሪ መሐንዲሶች ቀንና ማታ እየተፈራረቁ 24 ሰዓት ሥራቸውን እንደሚያከናውኑ ተናግረዋል፡፡

የጥራት ደረጃ ቁጥጥሩ ከግብዓት አቅርቦት ጀምሮ እያንዳንዱ ሥራ የተቀመጡ ዝርዝር መስፈርቶችን አሟልቶ ስለመሠራቱም በተዘጋጀ ቼክሊስት አማካኝነት ቁጥጥር እንደሚደረግ ገልጸዋል፡፡

አንዱ የሙሌት ንጣፍ አልቆ የሚቀጥለው ሲደረብ፤ በሚደረብበት ንጣፍ ላይ ፍሳሽ ውሃና ቆሻሻ አለመኖሩን ማረጋገጥ ፤ በሁለት ንጣፎች መካከል ጥብቅ ተያያዥነት እንዲኖር የሚያደርገው ማያያዣ አስቀድሞ መደረጉን መመልከት፤ ለሙሌቱ የሚውለው ኮንክሪት የሙቀት መጠን በሚፈለገው ደረጃ ልክ መሆኑን ማረጋገጥ፤ ጥቅጣቆው ጥብቅ መሆኑን በላብራቶሪ ፈትሾ ማረጋገጥ በቁጥጥር ሥራው ትኩረት ከሚሰጣቸው ጉዳዮች መካከል መሆናቸውን ጠቅሰዋል፡፡

በኮይሻ ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት የአማካሪው "ስታንቴክ" ድርጅት የኮንስትራክሽን ግብዓቶች ፍተሻ ቡድን መሪ ኢንጂነር አቡ ደጀኔ በበኩላቸው፤ ኮንክሪቱ ተብላልቶ ለሙሌት ከመቅረቡ በፊት የተፈጨው ድንጋይና አሸዋ በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት መመጠኑ ይረጋገጣል ብለዋል፡፡

እያንዳንዱ ግብዓትና የግንባታ ሥራ የጥራት ደረጃው ሳይንሳዊ በሆነ መለኪያ የሚረጋገጥ መሆኑንም ተናግረዋል፡፡ በሙሌቱ ወቅትም የተለያዩ ፍተሻዎች እንደሚደረጉና የጥቅጣቆው ጥብቅነትም በእነርሱም በኩል በላብራቶሪ የሚረጋገጥ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

የአማካሪ ድርጅቱን ወክለው የሚሠሩ ቢሆንም የግድቡን የጥራት ደረጃ ሲቆጣጠሩ እንደ አንድ ኢትዮጵያዊ ዜጋ በተቆርቋሪነት እና በባለቤትነት መንፈስ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

የኮይሻ ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት ሲጠናቀቅ እያንዳንዳቸው 300 ሜጋ ዋት የሚያመነጩ ስድስት ተርባይኖች ይኖሩታል።

# ዩኒቨርሲቲው ከ350 በላይ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

እያንዳንዱ እጽዋት ለየትኛው በሽታ መድኃኒትነት እንደሚያገለግሉ በመለየት ለእጽዋት መድኃኒቶቹ ሳይንሳዊ ስያሜ ተሰጥቷቸዋል ያሉት ዶክተር ከለላው፤ የዩኒቨርሲቲው ተመራማሪዎች በተፈጥሮ ሳይንስ በላብራቶሪ የታገዘ "የኬሚካል ካራክተራይዜሽን" የመለየት ሥራ እየሠሩ ነው ብለዋል፡፡

ዩኒቨርሲቲው የተሻሻሉ የእንሰት ችግኞችን በግቢው ውስጥ እና ከግቢው ውጪ ባሉ ቦታዎች ላይ በስፋት የማፍላት ሥራ በማከናወን ለማህበረሰቡ እያስተላለፈ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

የእንሰት እርሻን በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ወደሌሎች የአፍሪካ ሀገራት ለማስፋፋ እየተሠራ መሆኑን አስታውቀው፤ የተለያዩ አፍሪካዊያንን እንሰት በቀላሉ ለምግብነት መዋል እንደሚችል በጥናት ማረጋገጣቸውን ገልጸዋል።

እንሰት ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ቢመረት እንደሀገር የምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ አኳያ ከፍተኛ ፋይዳ ይኖረዋል ብለዋል፡፡ ዩኒቨርሲቲውም ይህን ታሳቢ አድርጎ ከተለያዩ ድርጅቶች ጋር እየሠራ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

የምግብ ዋስትና ጉዳይ በጣም ትኩረት የሚሻው በመሆኑ እንሰት ፋይዳው የጎላ መሆኑን ለማህበረሰቡ ማስተማርና እንሰትን እንዲያመርት ማድረግ ያስፈልጋል ሲሉ ዶክተር ከለላው አመላክተዋል፡፡

ከውጭ ተቋማት ጋር በጋራ እየተሠራ መሆኑን ጠቁመው፤ ጌሻ በተባለ ወረዳ ላይ ወደ 20 ሄክታር መሬት በእንሰት ለመሸፈን ታቅዶ እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

ዩኒቨርሲቲው አካታች የምርምርና ማህበረሰብ አቀፍ ሥራ በማከናወን ከማህበረሰብ አገልግሎት ጋር ተያይዞ በአትክልትና ፍራፍሬ በእንስሳት እርባታ የምርምር ግኝቶችን ወደ ውጤት በመለወጥ ለማህበረሰቡ እያሰራጨ መሆኑን ገልጸዋል።

እንደ ምክትል ፕሬዚዳንቱ ማብራሪያ፤ ዩኒቨርሲቲው የተለያዩ ፍራፍሬዎችን፣ አሳ፣ እንቁላልና ሌሎች ምርቶችን ያመርታል፡፡ በአሁኑ ወቅት ከሁለት ሺህ በላይ ዶሮዎች በግቢው ውስጥ በማራባት በቀን እስከ አንድ ሺ 900 እንቁላል ለማህበረሰቡ ያሰራጫል፡፡

ዩኒቨርሲቲው ከምርምር ሥራው ጎን ለጎን ለ54 አቅመ ደካሞች በየወሩ ድጋፍ እንደሚያደርግ አስታውቀው፤ በተጨማሪም በዘላቂነት 110 አረጋዊያን መኖር የሚችሉበት የመኖሪያ ማዕከል ግንባታ በመጠናቀቅ ላይ መሆኑን ምክትል ፕሬዚዳንቱ ተናግረዋል፡፡

በእነዚህና በሌሎች ጉዳዮች ዙሪያ ከለላው አዲሱ (ዶ/ር) ጋር ያደረግነው ሙሉ ቃለ ምልልስ በዛሬው የተጠየቅ አምዳችን ላይ ያገኙታል፡፡



ፎቶ፡- ሄዲ አብርሃ

ከለላው አዲሱ (ዶ/ር)

# ኢትዮጵያን በተለያዩ መስኮች ውጤታማ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በዘርፉ ቀዳሚ እንድትሆን በሁሉም ዘርፍ ሰው ሠራሽ አስተውሎትን በመጠቀም ውጤታማ ለመሆን መሥራት ይጠበቅብናል ብለዋል።

ሰው ሠራሽ አስተውሎት የሰው ልጅን የማሰብ፣ የማቀድ፣ የመማር፣ ምክንያታዊ የመሆን፣ የማመዛዘን፣ ቋንቋን የመረዳትና የአቅም ግንባታ ቀመርን ለማሽኖች በማስተማር በፍጥነትና በጥራት ለማከናወን የሚያስችል በመሆኑ ለዘርፉ ትኩረት በመስጠት መሥራት እንደሚገባ አስታውቀዋል፡፡

እንደ ኢንጂነር ወርቁ ገለጻ፣ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በሰው ሠራሽ አስተውሎት ማዕከል ግንባታ ያስተላለፉትን መልዕክት ከተቋማችን አልፎ በሀገሪቱ ለሚገኙት ተቋማት ታላቅ ብርታት ሆኗል ብለዋል፡፡ አሁን ላይ የኢትዮጵያ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት ሀገሪቱን በዘርፉ ተጠቃሚ ለማድረግ በርካታ ሥራዎችን እያከናወነ ይገኛል ሲሉ አብራርተዋል፡፡

ወጣቶችን ለማብቃት በክረምት መርሀ ግብር እስከ ሦስተኛ ዲግሪ ደረጃ ድረስ በማሰልጠን እውቀትና ክህሎታቸውን እንዲያጎለብቱ እያደረገ መሆኑን አስታውቀዋል።

በሀገራችን የፊልም ኢንዱስትሪ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የሰው ልጆችና በኢትዮጵያ የተሠሩ ሮቦቶች በትብብር "አስተውሎት" የተሰኘ በእውነተኛ ታሪክ ላይ የተመሠረተ ሳይንሳዊ ፊልም ሠርተው ለእይታ መብቃቱን ተናግረዋል።

ለምረቃ የበቃው "ፊልም በኢትዮጵያ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት እና በሰውኛ ፕሮዳክሽንና ኢንተርቴይመንት የተዘጋጀ ሲሆን፤ ዝግጅቱ አንድ ዓመት ተኩል የፈጀና ሙሉ በሙሉ በእውነተኛ ታሪክ የተመሰረተ ሳይንሳዊ ፊልም ነው ብለዋል።

በፊልሙ አንጋፋ ተዋንያን፣ ታላላቅ ሰዎችና ወጣት ተዋንያን መሳተፋቸውን ገልጸው፤ "አስተውሎት" ፊልም ለእይታ እስከሚቀርብ እገዛ ላደረጉ የጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት፣ ለኢትዮ ቴሌኮም፣ ለኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ ለብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት፣ ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ ለፌዴራል ፖሊስና ለሌሎች ተባባሪ ተቋማትና ግለሰቦች ምስጋና አቅርበዋል፡፡

በፊልሙ ምርቃት ላይ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)፣ የኢፌዴሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ተመስገን ጥሩነህ፣ የኢትዮጵያ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ወርቁ ጋቸና (ኢ/ር)፣ ሌሎች ከፍተኛ የመንግሥት ባለስልጣናት፣ የኪነ-ጥበብ ሰዎች እና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ተገኝተዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የሸዋል ኢድ የብዝሃነታችን ተጨማሪ ውበት !

በረመዳን የጾም ወር ማብቂያ ላይ ተጨማሪ ስድስት የጾም ቀናት ያሉ ሲሆን፣ የእነዚህን ቀናት መጠናቀቅ ተከትሎ የሸዋል ኢድ ይከበራል። የሸዋል ኢድ በድምቀት ከሚከበርባቸው አካባቢዎች መካለል ሐረርን የሚስተካከላት የለም። የሸዋል ኢድ ከ15ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ በሐረር መከበር እንደተጀመረ የታሪክ ድርሳናት ያስረዳሉ።

የሸዋል ኢድ በሐረሪዎች ዘንድ የሸዋል ጾም ከተጠናቀቀ በኋላ ለሦስት ተከታታይ ቀናት በድምቀት የሚከበር በዓል ነው። በዚህ በዓል በየትኛው ቦታ ያለ ሰው ወደ ሐረር መጥቶ ከቤተሰቡ ጋር የሚዘያየርበት እና ያላገቡ የሚተጫጩበት በዓል ነው። በዚህ በዓል የሚታደሙት በሐረር የሚኖሩ ሐረሪዎች ብቻ ሳይሆኑ፣ የብሔረሰቡ ተወላጅ ያልሆኑ እና በክልሉ የሚኖሩ፣ በመላው ኢትዮጵያ እና ከሀገር ውጪ የሚኖሩ ሐረሪዎች ይህንን በዓል ለመታደም ይሰበሰባሉ። ይህም የበዓሉ አንዱ ድምቀት ለመሆን በቅቷል። አሁን አሁን ደግሞ ከሁሉም ኢትዮጵያ ክፍል የመጡ ብሔር ብሔረሰቦች በሐረር በመገኘት የሸዋል ኢድን በጋራ እያከበሩት ይገኛሉ።

የሸዋል ኢድ ክብረ በዓል አከባበር የሚጀመረው ከዋናው በዓል ሁለት ቀን ቀደም ብሎ ነው። በሐረሪ ሸዋል ኢድ የባህል አልባሳቶች የሚወጡበት፣ ያላገቡ ሐረሪዎች በጌጣጌጦቻቸው የሚዋቡበት ልዩ ቀን ነው። የሸዋል ኢድ በዓል ወጣቶች በይበልጥ የሚግባቡበትና የሚተጫጩበት እንደሆነ፣ ይልቁንም የሐረር ወጣቶች ባህልና አኗኗራቸውን የሚያንጸባርቁበት አጋጣሚም ነው።

ሐረር የጀጎል ግንብ እና አምስቱ በሮች፣ የወርቅ ሳንቲሞች፣ ረጅም ዕድሜን ያስቆጠሩ መስጊዶች፣ የሥነ ሕንፃ፣ የታሪክን አሻራ የሚያንፀባርቁ የቤት ውስጥ ዕቃዎች ያሉባት የቱሪስት ማዕከል ነች። በዚህ እምቅ የቱሪስት ሀብቶቿ ላይ የሸዋል ኢድ በዩኔስኮ በማይዳሰስ ቅርስነት የዓለም ቅርስ አካል አድርጎ መመዝገቡ ለታሪኪቷ ከተማ ድርብ ግርማ ሞገስን አላብሷታል።

ኢትዮጵያ በተፈጥሮ የታደለችና በየትኛውም የሀገሪቱ ክፍል ስንሄድ ያልተነኩ እምቅ ሀብቶች በስፋት የሚገኙባት ሀገር ነች። እነዚህ የተፈጥሮ ሀብቶች በአግባቡ ከታወቁ እና ጥቅም ላይ መዋል ከቻሉም የኢትዮጵያ የብልጽግና መሠረትና የሕዝቦቿም የኑሮ መሠረቶች ይሆናሉ።

ከለውጡ ወዲህ መንግሥት አዳዲስ የቱሪስት መዳረሻ ግንባታዎች በስፋት በማከናወንና እና ለቱሪዝም ዘርፉ መጠናከር የማይተካ ሚና በመጫወት ላይ ይገኛል። እንደ ሀገርም መንግሥት ኢኮኖሚውን ወደ ፊት ያሻግራሉ ብሎ ተስፋ ከጣለባቸው የግብርና፤ኢንዱስትሪ፤ማዕድንና ቴክኖሎጂ ጋር በአንድነት የቱሪዝም ዘርፉ የመሪነት ሚና እንዲኖረው አድርጓል።

የቱሪዝም ቦታዎችን በማስፋትና በመንከባከብ እንዲሁም ለቅርሶች ተገቢው እንክብካቤ በመደረጉ ምክንያትም የሸዋል ኢድ አከባበር ሥርዓትን አከባበር ጨምሮ ኢትዮጵያ በዩኔስኮ የተመዘገቡ የቱሪስት መስህቦችን 16 በማድረስ በአፍሪካ ቀዳሚነቷን ማረጋገጥ ችላለች።

የሸዋል ኢድ በዓል በተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ የሳይንስና የባህል ተቋም (ዩኔስኮ) መመዝገቡ ኢትዮጵያ ብዝሃነት የሚንጸባረቅባት ሀገር መሆኗን ለዓለም ሕዝብ ለማሳየት ከማስቻሉም በላይ ሀገሪቱ በቱሪዝም ዘርፍ የሚደረገው እንቅስቃሴ እንዲጠናከርና አድማሱን እንዲያሰፋ የሚያደርግ ነው። ይህ ታሪካዊ ውሳኔም ሐረር ከተማን በዩኔስኮ ሁለት ቅርሶችን ያስመዘገበች ብቸኛዋ የሀገራችን ከተማ እንድትሆን አድርጓታል።

በመሆኑም ኢትዮጵያ ያላትን ዕምቅ የተፈጥሮ ሀብቶች በአግባቡ በማወቅ፣ በመጠቀምና በመጠበቅ ለትውልድ የሚተርፍ ሥራ መሥራት የእያንዳንዱ ዜጋ ግዴታ ሊሆን ይገባል። በየአካባቢው ያለውን እምቅ አቅም የተረዳ ዜጋ ለመገፋፋትና ለመጣላት የሚሆን ጊዜ ስለማይኖረው ያለንን እምቅ ሀብት ሥራ ላይ አውለን የኢትዮጵያን ብልጽግና ማረጋገጥ ለነገ ልንለው የምንችለው ተግባር አይደለም።

ከዚሁ ጎን ለጎንም ለቱሪዝም ዘርፉ እንቅፋት የሆነውን ጦርነትና ግጭት በማስወገድ ኢትዮጵያ ያላትን ዕምቅ የተፈጥሮ ሀብቶችን እንድትጠቀም ማድረግ ያስፈልጋል። በተባበሩት መንግሥታት የሳይንስ፣ ትምህርት እና ባህል ድርጅት/ዩኔስኮ/ በማይዳሰስ ቅርስነት አምስተኛ ሆኖ የተመዘገበው የሸዋል ኢድ ከሃይማኖታዊ አከባበሩ ባሻገር የኢትዮጵያዊያን ብዝሃነት የሚታይበት ቅርስ በመሆኑ ሃይማኖታዊና ባህላዊ ትውፊቱን ጠብቆ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲሸጋገር ማድረግ ይገባል!


አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል :- epa@press.et

ዋና አዘጋጅ
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

አድራሻ
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ
ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የኮሪደር ልማትና ሰው ተኮር ተግባራት

**እስማኤል አረቦ**

ስምና ግብር ለየቅል እንደሚባለው አዲስ አበባ ስሟን በማይመጥን ሁኔታ ለዘመናት ኖራለች። እንደ ስሟ አዲስ ሳትሆን ከእርጅናም በታች ወርዳ ተጎሳቁላ እና ነትባ ዘመናትን ተሻግራለች።

130 ዓመታትን ባስቆጠረው ቆይታዋ ወደ ፊት ከመጓዝ ይልቅ የኋሊት እየተጓዘች የከተሞች ጭራ ለመሆን በቅታለች። በተለይም መሃልኛው የአዲስ አበባ ክፍል ችምችም ብለው በተሰሩ ቤቶች የታጨቀ፤ ከዘመኑ ጋር ያልዘመነ፤ከ130 ዓመታት በፊት በነበረው የቀጠለ እና በአሁኑ ወቅት ያለውን የአኗኗር ሁኔታ የማይመጥን ነው። አብዛኞቹ ቤቶች አንድ መጸዳጃ ቤትን ለሰላሳ ፤ለአርባ የሚጠቀሙ ብዙዎችም መጸዳጃ ቤት የሌላቸውና በየጥጋጥጉ ለመጠቀም የተገደዱ ዜጎች ያሉባቸው አካባቢዎች ናቸው።

እነዚህ አካባቢዎች የአዲስ አበባን የኋሊት ጉዞ የሚያሳዩና የከተማዋ የድህነት መገለጫዎችም ናቸው። ጎዳና ተዳዳሪነት፤ሴተኛ አዳሪነት ፤ማጅራት መቺነት የመሳሰሉት ኢሞራላዊ እና ወንጀል ነክ ድርጊቶች የሚፈጸምባቸው ናቸው። ቁማር ቤቶች፤ጫት ቤቶች፤ሺሻ ቤቶችና አረቄ ቤቶች የእነዚህ አካባቢዎች መገለጫዎች ናቸው።

ፒያሳን የመሳሰሉ አካባቢዎች ስማቸው ገናና ቢሆንም በገቢር ግን ስማቸውን የሚመጥን ገጽታ የላቸውም። ምንም አይነት ዘመናዊነት የማይታይባቸው ኋላቀር አካባቢዎች ከመሆናቸውም በላይ በስመ አራዳ ለዘመናት ድህነት ተጭኗቸው የቆዩ ናቸው።

ስምና ግብር በተራራቀበት በእነዚህ አካባቢዎች ሰዎች በአንዲት ክፍል ውስጥ ቆጥና ምድር ሰርተው ፤መጸዳጃ ቤት ተጋርተው ፤በአንዲት ክፍል አስር፤ አስራ አምስት ሆነው ተደራርበውና ተነባብረው የሚኖሩባቸው የድህነት ጥግ የሚታይባቸው የከተማችን አካል ናቸው።

ይህ አልበቃ ብሎ አካባቢዎቹ በመሰረተ ልማት እጥረት የተጎዱ ናቸው። ለስሙ መሃል አካባቢ ይባል እንጂ የኤሌክትሪክ ዝርጋታው እጅግ ኋላቀር ከመሆኑ በላይ እጅግ የተወሳሰበና ለአደጋም የተጋለጠ ነው። በዚህ ላይ ዝናብና የንፋስ ሽውታ ሲያገኘው በቀላሉ የሚበጠስና መብራትም በየአጋጣሚው የሚጠፋበት አካባቢ ነው።

ከሁሉም የከፋው ደግሞ በእነዚህ አካባቢዎች ሲኖሩ የቆዩ ነዋሪዎች በቂ መጸዳጃ ቤቶች ሌላቸው፤በአንዲት ጠባብ ክፍል ተቆራምደው ለመኖር ተፈረደባቸውና ከሰው ልጅ አኗኗር ባፈነገጠ መልኩ በአንዲት ጠበብ ክፍል አባወራና እማ ወራ፤ልጆችና አለፍ ሲልም ዘመድ አዝማድ ታጉረው እንዲኖሩ የተፈረደባቸው ናቸው።

ይህ ከሰው በታች የሆነ ኑሮ አንድ ቦታ ማብቃት ስላለበት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከፌዴራል መንግሥት ጋር በመቀናጀት የከተማ መልሶ ማደስና ኮሪደር ልማት ፕሮጀክትን ይፋ አድርጓል። ይህ የመልሶ ማልማትና ኮሪደር ልማት ፕሮጀክት በአይነቱ አዲስ ሆነና ከፍተኛ ስፋት ያለውን ቦታ የሚሸፍን ነው።

በዚህ ልማት የሚካተቱት አካባቢዎች ከፒያሳ እስከ አራት ኪሎ፣ ከአራት ኪሎ እስከ ቦሌ ድልድይ፣ ከቦሌ ድልድይ በመገናኛ ወደ ሲኤምሲ፣ ከቦሌ ተርሚናል ወደ ጎሮ፣ ከሜክሲኮ ወደ ወሎ ሠፈር፣ እንዲሁም ከእንግሊዝ ኤምባሲ ወደ አራት ኪሎ የሚወስዱ ኮሪደሮች መሆናቸው ታውቋል። ስራውም በስድስት ወራት ውስጥ እንደሚጠናቀቅም የከተማዋ አስተዳደር ኃላፊዎች እየተናገሩ ነው።

እነዚህ ሥራዎች ሲከናወኑም ከተለያዩ ቦታዎች ለሚነሱ ግለሰቦች ምትክ ቦታ እየተሰጠ ነው። ቀደም ሲል በቀበሌ ቤት ውስጥ ለሚኖሩ ነዋሪዎች ከቦታው በመነሳታቸው ምክንያት ለችግር እንዳይጋለጡ ምትክ የቀበሌ ቤት ወይም ኮንዶሚኒየም እንደ ምርጫቸው እየተሰጣቸው ነው። በተመሳሳይም የግል ይዞታ የነበራቸው ነዋሪዎች ምትክ ቦታና ካሳ እንደሚሰጣቸው ተነግሯል። ይህም ተግባራዊ እየሆነ ነው።

የኮሪደር ልማቱ ገና በጥንስስ ላይ እያለ እና መተግበር ከጀመረ በኋላም የሚነዙ በርካታ አሉባልታዎች ነበሩ። በተለይም ድሃውን ከኖረበት ለማቀፈናቀል የተሸረበ ሴራ ነው፤የአዲስ አበባን ባህልና ተውፊት ለማጥፋት የታለመ ነው፤ ድሃዎችን ለማፈናቀል ነው ወዘተ የሚሉ አሉባልታዎች በስፋት ይነዙ ነበር። ሆኖም እውነትና ንጋት እያደር ይጠራል እንዲሉ ሳይውል ሳያድር ልማቱ በተቃራኒው በርካታ ትሩፋቶችን ይዞ መምጣቱን እያስመሰከረ ነው።

ለዘመናት በአንዲት ጠባብ ክፍል ይኖሩ የነበሩ ዜጎች ዛሬ ቀን ወጥቶላቸው ባለሁለትና ባለሦስት ክፍል ቤት አግኝተው እንደ ልባቸው መኖር ጀምረዋል። ቀደም ሲል ሻወር መውሰድ፤ንጹህ መጸዳጃ ቤት ማግኘት፤ንጹህ ማዕድ ቤት ማብሰል ቅንጦት ይመስል የነበረው ዛሬ ሁሉም በሚባል ደረጃ የዚህ እድል ተጠቃሚ ሆነዋል።

በተለይም በመልሶ ማልማቱ የተነሳው የፒያሳ አካባቢ ጎዳና ተዳዳሪነት፤ሴተኛ አዳሪነት ፤ማጅራት መቺነትና የመሳሰሉት ኢሞራላዊ እና ወንጀል ነክ ድርጊቶች የሚፈጸምባቸው የአዲስ አበባ አካባቢዎች ግንባር ቀደሙ ነው። ቁማር ቤቶች፤ጫት ቤቶች፤ሺሻ ቤቶችና አረቄ ቤቶች የእነዚህ አካባቢዎች መገለጫዎች ናቸው።

በእነዚህ አካባቢዎች መሸት ሲል በቀላሉ ወጥቶ መግባት አይቻልም። ማጅራት መመታት፤መሰረቅ፤መደፈርና የመሳሰሉት ድርጊቶች ሰርክ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ናቸው። እንኳን አዲስ ሆኖ እግር ለጣለው ሰው ቀርቶ ዘመናትን ለኖረ ሰው በእነዚህ አካባቢዎች በሰላም ወጥቶ መግባት ብርቅ ነው።

ከዚህ አሰቃቂ ህይወት የወጡ ሰዎችም ዛሬ ፈጣሪንና መንግሥትን ማመስገን ጀምረዋል። በልማቱ ተነስተው ወደ ሌሎች አካባቢዎች የሄዱ ነዋሪዎች «ቀን ወጣልን» ሲሉ ተደምጠዋል። ብዙዎቹ ነዋሪዎች የቀድሞው ኑሯቸውን ከጨለማ ጋር አመሳስለውታል።

በአንዲት ክፍል ለዘመናት ተጨቁነው የኖሩት እነዚህ ምስኪን ዜጎች ዛሬ ገበናቸው ተከቷል። የጋራ መኖሪያ ቤትም ሆነ ተገጣጣሚ ቤቶችን የመረጡ ዜጎች እንደ ሰው መተኛት፤እንደ ሰው በዘመናዊ ሻወር ለመታጠብ፤በሁለት በሦስት ክፍል ውስጥ መምነሽነሽ ፤በንጹህ መጸዳጃ ለመጠቀም በቅተዋል።

ከእነዚህ አካባቢዎች ተነስተው በተለያዩ አካካቢዎች የቤት እድል ባለቤት የሆኑት ዜጎች ዛሬ በሰላም ወጥተው ይገባሉ። ልጆቻቸውን ለተለያዩ ሱሶች ከሚያጋልጡ ድርጊቶች የራቁ ናቸው። ጽዳታቸውም በመልካም ሁኔታ የተጠበቀ ነው።

በአጠቃላይ የኮሪደር ልማቱ ለድሃዎች የመጣ ትሩፋት ነው ማለት ይቻላል። የተጎሳቆለውን አዲስ አበባ ገጽታ ለመቀየር ከማስቻሉም በላይ ለዘመናት በድህነት አረንቋ ውስጥ ተዘፍቀው የቆዩ ምስኪን ዜጎችን ከጨለማ ወደ ብርሃን ያወጣ ሥራ ነው። በተለይም ቀደም ባለው መንግሥት በመልሶ ማልማት ዙሪያ የነበረውን ኢ-ፍትሐዊ እና ሰብአዊ ድርጊት የሻረ እና የዜጎችም በልማት ላይ ያላቸውን እምነት ያረጋገጠ ነው።

ቀደም ባለው ዘመን አዲስ አበባ ከተማ በነባር መንደሮችና በማስፋፊያ አካባቢዎች የሚገኙ ነዋሪዎችን፣ እንዲሁም አርሶ አደሮችን አፈናቅላለች። በተለይ በቂ ምትክ ቦታና ካሳ ሳይከፈላቸው ተፈናቅለው ለከፋ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር የተጋለጡ በርካቶች ነበሩ። የመልሶ ማልማት ሥራ ነዋሪዎችን የሚያካትትና የሚያሳትፍ አልነበረም።

ዜጎች ፣ ከኖሩበት ጎስቋላ ኑሮ የሚያላቅቅና ወደ ተሻለ ደረጃ የሚያደርስ ሳይሆን የበለጠ ጉስቁልናን በሚያስከትል መልኩ ለባሰ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር የሚዳርግ ነበር።

ዛሬ ግን ሁኔታዎች ተለውጠው መልሶ ማልማትም ይሁን ኮሪደር ልማቱ በዝቅተኛ ኑሮ ህይወታቸውን ሲገፉ ለቆዩ ነዋሪዎች በርካታ ትሩፋቶችን ይዞ መጥቷል። ሰዎችን ከጨለማ ወደ ብርሃን የሚያወጣና በቀጣይም ዜጎች በመልሶ ማልማቱ እና የኮሪደር ልማቱ ላይ እምነት እንዲጥሉ የሚያደርግ ነው። ይህም ከነዋሪዎቹ ከራሳቸው አንደበት ተደምጧል።

# ተጠየቅ

## “ ተመራማሪዎች የትም መሄድ ሳያስፈልጋቸው በግቢ ውስጥ ምርምር ማድረግ የሚችሉበት አውድ ተፈጥሯል”

\- ከለላው አዲሱ (ዶ/ር)

የቦንጋ ዩኒቨርሲቲ የአካዳሚክስ ምርምር ቴክኖሎጂ ሽግግርና የማህበረሰብ አገልግሎት ምክትል ፕሬዚዳንት

**ሙሉቀን ታደገና ሞገስ ተስፋ**

**አንድ ዩኒቨርሲቲ ሲቋቋም ከመማር ማስተማሩ በተጨማሪ በአካባቢው ያለውን የመልማት ጸጋ ታሳቢ ያደረገ የምርምር ሥራዎችን በመሥራት የማህበረሰቡን የኑሮ ደረጃ እንዲሻሻል ማድረግ ነው። ከተመሠረተ ገና የስድስት ዓመት ዕድሜ የሆነው በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል የሚገኘው የቦንጋ ዩኒቨርሲቲ ከተቋቋመበት ዓላማና ግብ አንጻር ምን ሠራ? በተለይ ክልሉ ከፍተኛ የሆነ የተፈጥሮ ሀብት ያለው ከመሆኑ አኳያ እድሉን ከመጠቀም አንጻር ምን አከናወነ? በተለይም አካባቢው ከሚታወቅበት በቡና ልማት ዙሪያ ማህበረሰቡን ተጠቃሚ ያደረጉ ችግር ፈች ምርምሮችን ከመሥራት አንጻር ምን አከናወነ? ሲል በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የአዲስ ዘመን ጋዜጣ የመልካም አስተዳደርና የምርምራ ቡድን የቦንጋ ዩኒቨርሲቲ የአካዳሚክስ ምርምር ቴክኖሎጂ ሽግግርና የማህበረሰብ አገልግሎት ምክትል ፕሬዚዳንት ከለላው አዲሱ (ዶ/ር) ጋር ቆይታ አድርጓል። እንደሚከተለው አቅርቦታል።**



ፎቶ - ሐዲስ አብርሃ

**አዲስ ዘመን፡- ዩኒቨርሲቲው ሲመሰረት እንደማንኛውም ከፍተኛ የትምህርት ተቋም የራሱ የሆነ ሀገራዊ ተልዕኮ አለው። ከዚህ አንጻር ቦንጋ ዩኒቨርሲቲ ሲቋቋም ዋና ተልእኮው ምን ነበር?**

**ዶክተር ከለላው፡-** ማንኛውም የከፍተኛ የትምህርት ተቋም ሲመሰረት መማር ማስተማር፣ ምርምርና ማህበረሰብ አቀፍ አገልግሎት የሚሉትን ሶስት ዋና ዋና ተልዕኮዎች ይዞ ነው። ቦንጋ ዩኒቨርሲቲም የተመሰረተው እነዚህን ተልዕኮዎች ታሳቢ አድርጎ ነው።ዩኒቨርሲቲው የመማር ማስተማር ሥራ ከጀመረ ስድስት ዓመቱ ነው። በእነዚህ ዓመታት ሶስቱን ዋና ዋና ተልዕኮዎች በማስተሳሰር እቅዱን ማሳካት የሚችልበትን ስትራቴጂ በመንደፍ ወደ ሥራ ገብቷል።

ከመማር ማስተማር ተልእኮ አኳያ የዩኒቨርሲቲው ተማሪ የመቀበል አቅምና ውስጣዊ አደረጃጀቱ እየሰፋ መጥቷል። በ14 ፕሮግራሞች የመማር ማስተማር ሥራውን የጀመረው ዩኒቨርሲቲው የአካባቢውን ተጨባጭ ሁኔታና የመልማት ጸጋ በመገንዘብ የማህበረሰቡን ፍላጎት መሠረት ባደረገ መንገድ፣ ተገቢ በሆኑ የትምህርት ፕሮግራሞች ላይ የዳሰሳ ጥናት በማካሄድ አሁን ላይ 40 በሚደርሱ የቅድመ ምረቃ እና ሰባት የድህረ ምረቃ የትምህርት ፕሮግራሞችን እያስተማረ ይገኛል።እስካሁን በሶስት ዙር ተማሪዎችን አሰልጥኖ አስመርቋል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የመማር ማስተማርና ሌሎች ማህበረሰብ አቀፍ ሥራዎችን በቴክኖሎጂ አስደግፎ ከመሥራት አንጻር ዩኒቨርሲቲው ምን ያህል ዘምኗል?**

**ዶክተር ከለላው፡-** የትምህርትና ስልጠና ሥራዎችን የበለጠ ለማቀላጠፍ ፤ አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችንና መሠረተ ልማቶችን ከማስፋት አንጻር ሰፊ ሥራዎችን ሰርተናል፤ አገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓቱም ማንዋል ከሆነው አሰራር ወደ ዲጂታል አሰራር ተለውጧል። የተማሪ ምገባ ሥርዓት፤ የላይብረሪና የሪጂስትራል አገልግሎቶችን እንዲሁም የሠራተኛ የሰዓት መቆጣጠሪያ ጨምሮ በርካታ አገልግሎቶች በቴክኖሎጂ እንዲታገዙ ሆኗል።

የትምህርት አሰጣጡ ዓለማቀፋዊ ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን ለማስቻል ተማሪዎች በቀጥታ በአሜሪካ እና በአውሮፓ ሀገራት ከሚገኙ ፕሮፌሰሮች ትምህርት የሚያገኙበት እና በሴሚናሮች መሳተፍ የሚችሉበት ዘመናዊ የኦንላይን ቴክኖሎጂዎች ተግባራዊ ሆነዋል። ለዚህ ዓላማ ስምንት ስማርት የመማሪያ ክፍሎች ተገንብተዋል፤ አሁንም እየተገነቡ ያሉ ክፍሎች አሉ።

ተማሪዎች ያለምንም የኢንተርኔት ግንኙነት ስማርት ስልኮቻቸውን ተጠቅመው በሶስት ኪሎ ሜትር ራዲየስ ውስጥ የማጣቀሻ መጻሕፍቶችን በቀላሉ ማግኘት የሚያስችላቸው የቴክኖሎጂ ሥርዓት ተመቻችቷል። ምግብ ቤት ለመመገብ ሲሄዱ በወረቀት ሳይሆን በፊት ምልከታ ብቻ ራሳቸውን እያሳዩ እንዲገቡ ተደርጓል። አስተማማኝ የሆነ የኢንተርኔት አገልግሎት በግቢው ውስጥ አለ። ተማሪዎች እና መምህሮቻቸው ማንኛውም ሥራ በኦንላይን ለመተግበር አይቸገሩም።

**አዲስ ዘመን፡- አካባቢው ያለውን የተፈጥሮ ሀብት ያገናዘበ ምርምሮችን ከማከናወን አንጻር ዩኒቨርሲቲው ምን እየሰራ ነው?**

**ዶክተር ከለላው፡-** ከመማር ማስተማር ሥራዎች በተጓዳኝ የምርምርና ማህበረሰብ አቀፍ አገልግሎት አንዱ የዩኒቨርሲቲው ተልእኮ ነው። ስለዚህ በተለይ ከመማር ማስተማር ጋር ተያይዞ ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ ባሉት ጊዜያቶች የምርምርና የማህበረሰብ አቀፍ ሥራዎችን በተሳለጠ መንገድ ለማስኬድ በመጀመሪያ ደረጃ ችግሮች መለየት ነበረባቸው። ከዚህ አኳያ አካባቢው ላይ ምን ችግር አለ? የሚለውን ለመለየት የምርምር ባለሙያዎች ችግሮችን በጥናት እንዲለዩ ስምሪት ተደርጎ እንዲጠና ተደርጓል።በ12 ወረዳዎች ላይ ጥልቅ የሆነ የችግር ልየታ የዳሰሳ ጥናት በማድረግ ችግሮችን የመለየት ሥራዎች ተከናውነዋል።

80 በመቶ የሚሆነው የሀገሪቱ ማህበረሰብ የሚተዳደረው በግብርና ነው። በመሆኑም ችግሮቹ እንደ ሀገር ዘርፈ ብዙ ናቸው። ከዚህ አንጻር በክልሉ ያሉ ችግሮች መነሻቸው ምንድን ነው? በሚለው ላይ ማህበራዊ፤ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊውን ሁኔታ ሁሉ የሚያስተሳስር የልየታ ጥናት በማድረግ የመተንተን ሥራዎች ተሰርተዋል።በተለይ በዘጠኝ የዋና ዋና የትኩረት መስኮቸ ላይ ችግሮችን ለይቶ ለማስቀመጥ ተሞክሯል። ችግሮች በጣም ዘርፈ ብዙ ስለሆኑ ዘጠኙን በአራት ዋና ዋና መስኮች በመለየት በቅደም ተከተል በማስቀመጥ ቅድሚያ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገባቸውን ችግሮችን መለየት ተችሏል።

**አዲስ ዘመን፡- በአካባቢው ያለውን የተፈጥሮ ጸጋ ወደ ልማት ለመቀየር ምን እየሰራችሁ ነው ?**

**ዶክተር ከለላው፡-** በምርምርና ማህበረሰብ አቀፍ አገልግሎት የአካባቢውን የተፈጥሮ ጸጋ ከሀገራዊ አቅጣጫ ጋር በማስተሳሰር ወደ ልማት ለመቀየር የሚያስችሉ የትኩረት መስኮችን የመለየት ሥራዎች ተሰርተዋል።እንደሚታወቀው አካባቢው በተፈጥሮ ሀብት በጣም የታደለ ነው። በደን እና በእንስሳት እንዲሁም ከግርብና ጋር በተገናኙ ሀብቶች በጣም የበለጸገ ነው፡፡

ነገር ግን ሙሉ በሙሉ ጥቅም ላይ ባለመዋላቸው የማህበረሰቡ ኑሮ እዚህ ግባ የሚባል አይደለም።ይህን ሀብት በሚገባ አልምቶ መጠቀም ቢቻል የተሻለ ኑሮ መኖር የሚችልበት ሰፊ እድልና አጋጣሚ አለ።ለምሳሌ «ከአግሮ ኢኮሎጂ» አንጻር በዚህ አካባቢ ሁሉም ዓይነት አግሮ ኢኮሎጂ አለ። ስለዚህ ከግብርና አንጻር የተለያዩ የሰብል ዓይነቶችን ለማምረት ምቹ እድል አለ። ይህም ክልሉን በጣም ሰፊ የግብርና አቅም እንዲኖረው አድርጎታል።በነገራችን ላይ በዓለም አቀፍ ደረጃ በዩኔስኮ የተመዘገበው ዓለም አቀፍ «ባዮስፌሪ» ዘርፍ በዚህ ክልል የሚገኝ ነው። በዩኒቨርሲቲው ወደ አካባቢው ሲመጣ እነዚህን ሁሉ ዕድሎች በመጠቀም በአግባቡ የማህበረሰቡን ሕይወት ለማሳደግ አስቦ ነው።

ዩኒቨርሲቲው በመጀመሪያ ትኩረት አድርጎ የሠራው ትምህርት ላይ ነው።ስለሆነም እንደ ሀገር በትምህርቱ ዘርፍ መንግሥትን ከመደገፍ እና የሚስተዋሉ ክፍተቶችን ከመዝጋት አኳያ በተለይ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የትምህርት ጥራት ላይ በርካታ ሥራዎች ተሰርቷል። የትምህርት አሰጣጡ በጥራትና በተግባር ተደግፎ የሚሰጥበትን አግባብ ከተለያዩ ድርጅቶችና ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ውጤት ተኮር የሆነ ሥራዎችን አከናውነናል።

«ካማራ ኢዱኬሽን» ከሚባል ድርጅት ጋር በመተባበር 42 ለሚሆኑ ትምህርት ቤቶች ለእያንዳንዳቸው 25 ኮምፒውተሮችን ሰጥተናል። ኮምፒውተሮቹ በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት የሚሰጡ የትምህርት ዓይነቶች የተጫኑባቸው ናቸው።በዚህም ተማሪዎችን ለመደገፍ ጥረት ተደርጓል።ከከፋ ዞን ውጭ ሸካ፤ ኮንታና ቤንች ሸኮ እና ምዕራብ ኦሞ ድረስ ዲጂታል ቤተመጽሐፍ ተደራሽ ሆኗል።

በ12ኛ ክፍል ሀገር አቀፍ ፈተና የተሻለ ውጤት ያስመዘገቡ የክልሉ ተማሪዎችን ወደ ዩኒቨርሲቲው በመጥራት በየዓመቱ የማበረታቻ እውቅና ይሰጣል።ይህም ለሌሎች ተማሪዎች የሞራል መነሳሳት ከመፍጠር ባሻገር ዘርፈ ብዙ ትርጉም ያለው ነው ።

> “
> **በዚህ ዓመት 37 የሚሆኑ ተማሪዎችን በመጀመሪያ እና 10 የሚሆኑ ደግሞ በሁለተኛ ዲግሪ ለመጀመሪያ ጊዜ በቡና ሳይንስ የትምህርት ክፍል ያስመርቃል**

**አዲስ ዘመን፡- በትምህርት ዘርፉ ሆነ በአጠቃላይ ከተልእኮው አኳያ በተጨባጭ ምን ውጤት እየተገኘ ነው ?**

**ዶክተር ከለላው፡-** ለምሳሌ ቀድሞ በነበረው የትምህርት ሥርዓት በክልሉ ባሉ ዞኖችና ወረዳዎች በብሔራዊ ፈተና ምንም ዓይነት ተማሪ የማያልፍባቸው ትምህርት ቤቶች ነበሩ።ዩኒቨርሲቲው ድጋፍ ከጀመረ ጊዜ ጀምሮ ግን በጣም የተሻለ ቁጥር ያላቸው ተማሪዎች ማትሪክን ማለፍ ችለዋል።

ከትምህርት ዘርፉ ባሻገር ዩኒቨርሲቲው ከምርምር አንጻር ዋናው የትኩረት መስኩ ግብርና እና ተፈጥሮ ሀብት ላይ ነው። በተጨማሪም ጤና እና ማህበራዊና መሰል ዘርፎች የሚያከናውናቸው ሥራዎች አሉ።በዋናነት ምርትና ምርታማነት ማሻሻል አለብን በሚል ማህበረሰቡን የማስተማርና የመለወጥ ሥራዎችን ትኩረት ሰጥተን እየሰራን ነው። በዚህ ዘርፍ ምርምሮች ተጀምረዋል። ምርምሮቹ ተግባራዊ ምርምሮች ናቸው።

ምርምሮችን ለመሥራት የመጀመሪያው ሥራ ምርምር የሚከናወንበትን ቦታ መለየት ነው። የመጀመሪያው አመራጭ የዩኒቨርሲቲውን ግቢ ማየትና መጠቀም ነው። ዩኒቨርሲቲው ወደ 2 መቶ ሺ ካሬ ሜትር መሬት አለው።የግቢውን የመሬት አቀማመጥ መሰረት ያደረገ ሥራዎች ተሰርተዋል። ግብርና ላይ የሚሰራው የግብርና የምርምር አንዱ እና ግንባር ቀደሙ ነው። በዩኒቨርሲቲው ካለን መሬት በተጨማሪ ከወረዳ አስተዳደሮች ጋር በመነጋገር በተለያዩ ወረዳዎች ላይ መሬቶችን የማግኘትና ከህብረተሰቡ ጋር በቅርበት የምርምር ሥራዎን በመሥራት ማህበረሰቡን በተግባር እያስተማርን እንገኛለን።

ግቢው ውስጥ ያሉ ቦታዎችን መጠቀም ስለሚያስፈልግ ምን ምን ጉዳዮችን እንስራ በሚል ሃሳብ በተለይም አካባቢው በሚታወቅባቸው እንደ ቡና፤ ማር፤ ቅመማ ቅመም፤ ላይ ትኩረት ማድረግ

**ወደ ገጽ 7 ዞሯል**

# ተጠየቅ

## “ ተመራማሪዎች የትም መሄድ ሳያስፈልጋቸው በግቢ...

ከገጽ 6 የዞረ

አለብን ብለን፣ በሳይንሳዊ መንገድ ሥራዎችን በመሥራት እውቀት የማሸጋገር ተግባራትን አከናውነናል።

**አዲስ ዘመን፡- ዩኒቨርሲቲው በተጨባጭ ወደ ውጤት የተቀየሩ የምርምር ሥራዎችን ማከናወኑን ገልጸዋልናል፣ ዋና ፋይዳቸው ምንድን ነው?**

**ዶክተር ከሰላው፡-** በዋናነት አራት ፋይዳዎች አሉት። እነዚህም ምርምር አንዱ ሲሆን ተመራማሪዎች የትም መሄድ ሳያስፈልጋቸው በግቢው ውስጥ በቀላሉ ተግባራዊ ምርምር ማድረግ የሚችሉበት አውድ ተፈጥሯል። ተማሪዎች በዩኒቨርሲቲው እየኖሩ የሚመራመሩበት (living laboratory) አላቸው። በንድፈ ሃሳብ የተማሩትን በተግባር እያዩት፤ እየነኩና እየዳሰሱ የሚማሩበት ተቋም ነው። ለምሳሌ የእንስሳት ሀብት ትምህርት ክፍል ተማሪዎች በወተት ሀብት ልማት ሥራ፤ የበግ እርባታ፤ የከብት ድለባና ሌሎች ተያያዥ መስኮች ላይ ከዩኒቨርሲቲው መውጣት ሳይጠበቅባቸው እዚሁ በተግባር ይማራሉ፡፡

በተመሳሳይ አካባቢው የቡና መገኛ እንደመሆኑ መጠን ማህበረሰቡም ሕይወቱን ከመሰረተባቸው ዘርፎች ቡና አንዱ ነው። በመሆኑም ዩኒቨርሲቲው የቡና አመራረት ዘዴዎችን ለማዘመን በቡና ላይ የምርምር ተግባራትን ከማከናወን ባለፈ፣ በትምህርት ዘርፉም በመጀመሪያ እና በሁለተኛ ዲግሪ በቡና ዙሪያ ትምህርት የሚሰጥ የቡና የትምህርት ክፍል ከፍቷል። በዚህ ዓመት 37 የሚሆኑ ተማሪዎችን በመጀመሪያ እና 10 የሚሆኑ ደግሞ በሁለተኛ ዲግሪ ለመጀመሪያ ጊዜ በቡና ሳይንስ የትምህርት ክፍል ያስመርቃል፡፡

ቡና እንደ ሀገር ያለው ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ የሚታወቅ ነው።ነገር ግን የቡና መገኛ ሆነን እያለ ከምርትና ምርታማነት አንጻር ሌሎች ብዙ ሀገራት ኢትዮጵያን የቀደሙበት አግባብ አለ። የቡና መነሻ ኢትዮጵያ ሆና እያለች ከእኛ በተሻለ በጥራት በማምረት ለዓለም ገበያ እያቀረቡ ያሉ ሀገራት አሉ። ይህ ደግሞ ዘርፉ ሳይንሳዊ በመሆኑ አሰራር ባለመታገዙ ነው።

በተገቢው መንገድ እንደ ሀገር በቡና ዘርፉ በካበተ እውቀት ያዳበሩና የተካኑ ባለሙያዎች ሊኖሩ ይገባል። ቡና የማያመርቱ እንደ ጣሊያን ያሉ ሀገሮች ሳይቀር በቡና ዙሪያ ሳይንሳዊ ትምህርት ይሰጣሉ። ይህንን እውን ለማድረግ ዩኒቨርሲቲው በዘርፉ በቂ ባለሙያ እንዲኖሩ ለማስቻል ከፍተኛ ሥራዎችን እየሰራ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በቡና ሳይንስ የሰለጠኑ ባለሙያዎችን በዘርፉ ከተሰማሩ ድርጅቶችን ጋር ለማስተሳሰር ምን እየሰራችሁ ነው?**

**ዶክተር ከሰላው፡-** የቡና መገኛ ሀገር እንደመሆናችን መጠን ዘርፉን በሚገባ አውቆና ተረድቶ የተሻለ ሀገራዊ ተጠቃሚነትን ለመፍጠር እየሰራን ነው።ለዚህም በቡና መስክ ስፔሻላይዝ ያደረገ ባለሙያ ማፍራት ወሳኝ ነው።ይህንን እውን ለማድረግ ወደ ሥራ ገብተናል። አሁን ላይም በርካታ የቡና ድርጅቶች የቡና ሳይንስ ተማሪዎችን ለመቅጠር ጥያቄ እያቀረቡ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ዩኒቨርሲቲው በራሱ ገቢን ከማመንጨት አንጻር ምን እየሰራ ነው?**

**ዶክተር ከሰላው፡-** ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ ደረጃ እየሰራባቸው ካሉ መሰኮች ገቢ ማመንጨት አንዱ ነው። እንደ ሀገር ከከፍተኛ ተቋማት ጋር ተያይዞ የሪፎርም ሥራዎች እየተሰሩ ነው። ከእነዚህ የሪፎርም ሥራዎች ደግሞ አንደኛው ዩኒቨርሲቲዎች ራስ ገዝ መሆን አለባቸው የሚል ነው። ራስ ገዝ ለመሆን ደግሞ ዩኒቨርሲቲዎች የራሳቸውን ሀብት ማፍራትም አለባቸው።ራስ ገዝነት ደግሞ ብዙ እድሎች ያሉት፣ ይህም በብዙ መንገድ የሚታይ ነው። ከእነዚህ መካከል አንዱ ፋይናንስ በማመንጨት የፋይናንስ ነፃነትና አቅም መፍጠር ነው።

አሁን እንደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተቀመጠው አቅጣጫ በሚቀጥሉት አስር ዓመታት ውስጥ ዩኒቨርሲቲዎች ቢያንስ ግማሽ ያህሉን ዓመታዊ ገቢያቸውን በራሳቸው መሸፈን አለባቸው የሚል ነው። ይህን ለማሳካት ከወዲሁ መሥራት ካልተቻለ ስኬታማ መሆን ፈታኝ መሆኑ አይቀርም። ከዚህ አኳያ አሁን ላይ የቦንጋ ዩኒቨርሲቲ በራሱ እያስገኘ ያለው ገቢ ቀላል አይደለም። ወተት እናመርታለን፣ የተከልነው ቡና ምርት መስጠት ጀምሯል፤ ፍራፍሬ ላይ በተለይም ከአናናስ እና ከሙዝ ላይ ከፍተኛ ገቢ እያገኘን ነው።

እዚህ ላይ መረዳት የሚገባን ከዚህ ቀደም ሙዝ እና አናናስ በአካባቢው አያታወቁም ነበር። ነገር ግን እነዚህ



**ተማሪዎች ያለምንም የኢንተርኔት ግንኙነት ስማርት ስልኮቻቸውን ተጠቅመው በሶስት ኪሎ ሜትር ራዲየስ ውስጥ የማጣቀሻ መጻሕፍቶችን በቀላሉ ማግኘት የሚያስችላቸው የቴክኖሎጂ ሥርዓት ተመቻችቷል**

ፍራፍሬዎችን በማምረት ገቢ ማስገባት ተችሏል። ይህም ከዩኒቨርሲቲው ገቢው ባሻገር ለአርሶ አደሮች ተሞክሮ መስጠት የቻለ ነው። ዩኒቨርሲቲው የተሻሻለ የሙዝ ዝርያ ማህበረሰቡ የሚያገኝበትን መንገድ ፈጥሯል። ሙዝ ላይ የተሻሻሉ ዝርያዎችን በማምጣት በመትከል፤ ክትትል እና ድጋፍ በማድረግ የተሻለ ውጤት ተገኝቷል። ይህንን ምርት ወደ ውጭ እያወጣን ለማህበረሰቡ ተደራሽ እያደረግን ነው።ወተትም እና አናናስም እንደዚያው ነው።

**አዲስ ዘመን ፡- የዩኒቨርሲቲዎች አንዱ ተልእኮ የማህበረሰብ አቀፍ ሥራዎችን ማከናወን ነው፤ ከዚህ አኳያ ምን ተሰርቷል ?**

**ዶክተር ከሰላው፡-** ከማህበረሰብ አገልግሎት ጋር ተያይዞ ከፍተኛ ሥራዎችን እየሰራ ነው። ዩኒቨርሲቲው ቀደም ብዬ እንዳነሳሁት ፍራፍሬ ፣ አሳ ፣ እንቁላል እና ሌሎች ምርቶችን ያመርታል። አሁን ከ2000 በላይ ዶሮዎች አሉት። በቀን እስከ 1900 እንቁላል ይመረታል።እነዚህን ምርቶች አንድም ለዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ በተመጣኝ ዋጋ ይሸጣል።ከዛም ባለፈ ሥራ የሌላቸው ሴቶች አንድ ላይ በማደራጀት የሽያጭ ማዕከላትን በመገንባት ሸጠው እንዲጠቀሙ ያደርጋል።

እነዚህ የተደራጁ ሴቶች ወተቱንም፤ እንቁላሉንም፤ አናናሱንም በተመጣጣኝ ዋጋ ይወስዱና የተወሰነ ዋጋ ጨምረው ለማህበረሰቡ ይሸጣሉ። በዚህ ውስጥ ሁለት ነገሮችን አሳክተናል። አንደኛው የሥራ እድል ፈጥረናል። ሁለተኛው ደግሞ ማህበረሰቡ ከዚያ በፊት በቀላሉ የማያገኛቸውን ምርቶች በቀላሉ በአቅራቢያው እንዲያገኝ አድርገናል።

ከዚህ ውጭ ጎባ በሚባል ቆላማና ለም አፈር በሚበዛበት አካበቢ የሰሊጥ፤ ጤፍ፤ ማሾ የሚባሉ ዝርያዎችን በስፋት አምርተናል። ሞሪንጋ፤ ካሳቫ የመሳሰሉትንም በስፋት እንዲለሙ አድርገናል።ያመረጥነውን ሰሊጥ “በኢሲኤክስ” አንድ ዙር ሸጠናል። የተመረተው ሰሊጥ ሳይንሳዊ ዘዴን የተከተለ ስለነበር ምርት ገበያ ላይ አንደኛ ደረጃ መውጣት የቻለ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ዩኒቨርሲቲው “ሴትስ ፊድ አፍሪካ” የሚል ፕሮጀክት አስጀምሮ ነበር ። ይህ ፕሮጀክት ምን ላይ ደረሰ?**

**ዶክተር ከሰላው፡–** እንሰት በደቡብ አካባቢ በስፋት የሚታወቅ እና የሚመረት ነው። በትንሽ ቦታ ላይ ብዙ ምርት ያስገኛል። አንድ እንሰት በጣም ብዙ ሰው ይመግባል ፤ ድርቅንም ይቋቋማል። ስለዚህ እንሰትን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ቢመረት እንደ ሀገር የምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ አኳያ በጣም ከፍተኛ ፋይዳ ይኖረዋል። ዩኒቨርሲቲውም ይህን ታሳቢ አድርጎ ከተለያዩ ድርጅቶች ጋር እየሰራ ነው።

ይሁን እንጂ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ማህበረሰባችን ቡና እና መሰል ተክሎችን በስፋት በመትከል እንሰትን ማምረት ላይ የመቀዛቀዝ አዝማሚ እያሳየ ነው።ይህ ልክ አይደለም። ምክንያቱም የምግብ ዋስትና ጉዳይ በጣም ትኩረት የሚሻው ነው። ከዚያ አንጻር ፋይዳው የጎላ ስለሆነ ይህንን ለማህበረሰባችን ማስተማር እና ወደ እንሰት አምራችነቱ መመለስ ያስፈልጋል።

የእንሰት እርሻን በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ወደ አፍሪካ ሀገራት ለማስፋፋት እየሰራን ነው።በዚህም ከኢትዮጵያዊን ባለፈ አፍሪካዊያንን በቀላሉ መመገብ እንደምንችል በጥናት አረጋግጠናል። በዚህ ረገድ እኛ ጋር የተሻሻሉ የእንሰት ችግኞችን በስፋት በግቢ ውስጥ እና ከግቢው ውጭ ባሉ ቦታዎች ላይ የማፍላት ሥራ ተሰርቷል።

እነዚያን ችግኞች ለማህበረሰቡ እያስተላለፍን ነው።ጌሻ በተባለ ወረዳ ላይ ወደ 20 ሄክታር መሬት በእንሰት ለመሸፍን ታቅዶ እየተሰራ ነው።ሥራውን እንደ ፋኦ (Food and Agriculture Organization) ካሉ ዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር በጋራ እየሰራን ነው።ፋኦ በዚህ ጉዳይ ላይ መግባቱ ጥሩ ነው።ምክንያቱም ወደ አፍሪካ ሀገራት የማስፋፋት ስትራቴጂክ እቅዳችንን ቀላል ያደርገዋል።

**አዲስ ዘመን፡- በአካባቢያችሁ ሰፋፊ የእርሻ ድርጅቶች ይገኛሉ።ከእነሱ ጋር ተባብሮ ከመሥራት አኳያ ምን እያደረጋችሁ ነው?**

**ዶክተር ከሰላው፡-** በአካባቢያችን በርካታ ሰፋፊ የእርሻ ሥራዎችን የሚያከናወኑ ድርጅቶች አሉ።ለምሳሌ አንዱ ውሽ ውሽ የሻይ ቅጠል ነው። ከውሽ ውሽ ሻይ ጋር አብሮ ለመሥራት የሚያስችል የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርመናል።ሻይ ላይ እኛ ላይ እየሞከረነው ያለው ነገር አለ።

ሌላው ተማሪዎቻችን ኢንትርን ሺፕ እዚያ ሂደው ይማራሉ። ምሩቃኖቻችን እዛ ሄደው ይሰራሉ።ለምሳሌ በዘንድሮው ዓመት 15 የሚሆኑ ምሩቃን እዚያ እንዲቀጠሩ ተደርጓል። ጉመሮ እና ጨዋቃ የሚባሉ አሉ። በእነዚህ ተቋማት ተመራቂዎቻችን ሄደው እንዲሰሩ ማድረግ ተችሏል።ይህ ዩኒቨርሲቲው በአካባቢው ከሚገኙ የእርሻ ተቋማት ጋር የሚያደርገው ትስስር ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ዩኒቨርሲቲው ለሚያደርጋቸው የምርምር ሥራዎች የሚያስፈልገውን ወጪ የሚሸፍነው እንዴት ነው ?**

**ዶክተር ከሰላው፡-** እኛ በመጣንበት አጭር እድሜ አኳያ የምርምር ሥራዎችን በተፈለገው ልክ መሥራት የቻልነው ከመንግሥት በምናገኘው በጀት ብቻ ነው። አሁን ላይ ምርምርን በውስጥ ገቢ ብቻ ማከናወን ከባድ ነው።የውጭ የገንዘብ ድጋፍ ያስፈልጋል። ይህ ምናልባትም ከዩኒቨርሲቲው ዕድሜ ጋር የሚገናኝ ሊሆን ይችላል።

በነገራችን ላይ ከመንግሥት የሚገኘውን በጀት በትክክል ምንም ሳይባክን ሥራ ላይ ከዋለ ብዙ ሥራዎችን መሥራት ይቻላል።ይህን ከማድረግ አንጻር የቦንጋ ዩኒቨርሲቲ ውጤታማ ነው ብዬ አስባለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- አካባቢው በተለያዩ እጽዋት የተሞላ እንደመሆኑ መጠን ባህላዊ የመድኃኒት ቅመማን በምርምር በማስደገፍ ዘመናዊ ከማድረግ አንጻር ምን እየሰራችሁ ነው?**

**ዶክተር ከሰላው፡-** ይህ ዩኒቨርሲቲው እያከናወናቸው ከሚገኙት 17 ፕሮጀክቶች መካከል ሀገር በቀል የመድኃኒት እውቀቶችን ማዘመን የሚለው አንዱ ነው። በዚህ ላይ ሥራዎች እየተሰሩ ነው። ከባህል መድኃኒትነት ጋር ተያይዞ ሀገር በቀል እውቀቶች አሉ። ከዚህ አንጻር የመጀመሪያው ያለው ሀብት ምንድን ነው? የሚለውን መለየት ነው።

አካባቢው በእጽዋት የታደለ ስለሆነ መድኃኒትነት ያላቸው እጽዋቶች በብዛት ይገኛሉ። እነዚህ ተጠቅመው ደግሞ በባሕላዊ መንገድ በሽታን የሚያድኑ የሀገር በቀል እውቀት ባለቤት የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች አሉ።እነዚህ ሰዎች እያንዳንዱ እጽዋት ለየትኛው በሽታ እንደሚውል ያውቃሉ።ከ350 በላይ የሚሆኑ እጽዋት ተለይተው በአንድ ማዕከል ውስጥ እንዲበዙ እና እንዲቀመጡ በማድረግ የምርምር ሥራዎች እየተከናወኑ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ እናመሰግናለን፡፡**

**ዶክተር ከሰላው፡-** እኔም አመሰግናለሁ፡፡

ኢኮኖሚ

# ንግድና ግብይት

# የፋይናንስ አቅርቦትን ማሻሻል- የግሉን ዘርፍ ለማጠናከር

**ፍሬሕይወት አወቀ**

በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ ትልቅ ድርሻ ያለው የንግዱ ማህበረሰብ በሥራ ዕድል ፈጠራ፣ የሀገሪቱን ገቢና የውጭ ምንዛሪ በማሳደግ እንዲሁም አጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት እንዲጨምር በማድረግ ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከተ ይገኛል።ይህም ሚናው እየጨመረ የመጣው ሲሆን፣ አሁንም ሚናው የበለጠ እንዲጎለብት ለማድረግ የፖሊሲ ማሻሻያዎችን ከማድረግ አንስቶ የፋይናንስ ድጋፎችን ማድረግ ከመንግሥትና ከሚመለከታቸው አካላት እንደሚጠበቅ ይታመናል።

ይሁንና በአሁኑ ወቅት ለንግዱ ማህበረሰብ ወሳኝ ሚና ያለው የፋይናንስ አቅርቦት እጥረት የዘርፉ ዋነኛ ማነቆ መሆኑን የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ያስጠናው ጥናት አመላክቷል።ምክር ቤቱ ከሰሞኑ "የብድር አቅርቦት ፋይዳ ለቢዝነስ" በሚል መሪ ሃሳብ ከባንክና የፋይናንስ ተቋማት፣ ከንግዱ ማህበረሰብ እና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት አካሂዷል። ውይይቱም ችግሩን በመለየት የመፍትሔ አቅጣጫ ለማስቀመጥ ጠቃሚ እንደሆነ ተጠቁሟል።

በውይይቱ የንግዱ ዘርፍ ለሀገራዊ ምጣኔ ሀብት ዕድገት ያለውን ሚና አሟጦ መጫወት እንዲችል ማነቆ የሆነበትን ይህን የፋይናንስ አቅርቦት እጥረት መቅረፍ የግድ መሆኑ ተገልጿል።ችግሩን በልኩ የተረዳው የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የፋይናንስ አቅርቦቱን እጥረት ምክንያት ማወቅ የመፍትሔ ግማሽ ነው እንደሚባለው የንግዱ ማህበረሰብ ያለበትን ችግር ለመለየት የሚያስችል ጥናት ማስደረጉ ተጠቅሷል።ጥናቱ እንዳመላከተው፤ የንግዱ ዘርፍ ማነቆ ከሆኑ ጉዳዮች መካከል የፋይናንስ አቅርቦት እጥረት 40 በመቶ ድርሻ ያለው መሆኑ አለው፡፡

በተለያዩ የንግድ ዘርፎች የተሰማሩት የንግዱ ማህበረሰቦች ካነሷቸው ችግሮች መካከል የብድር አቅርቦት ትልቁ ሆኗል።ከፋይናንስ አቅርቦት በተጨማሪ የተለያዩ ችግሮች እንደሚያጋጥሟቸው አመልክተው፣ የንግድ ሥራቸውን ለማቀላጠፍ የፋይናንስ አቅርቦት ወሳኝ እንደሆነ አስታውቀዋል።የብድር አቅርቦት እጥረት ትልቁ ፈተና ነው ሲሉም ተናግረው፣ ነጋዴው ከባንክ ብድር ለማግኘት የሚወስደው ጊዜ ረዘም ያለ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በንግድ ሥራው ላይ ተጽዕኖ እያሳደረ መሆኑን ገልጸዋል።

የአዲስ አበባ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ከንግዱ ማህበረሰብ ጋር በመሆን በተለያየ ጊዜ የተለያዩ መድረኮችን በማዘጋጀት ሲሰራ መቆየቱን ጠቅሰው፤ በተለይም በአሁኑ ወቅት የብድር አቅርቦት እጥረት በንግዱ ማህበረሰብ ላይ እያደረሰ ያለውን ጫና ለመከላከል ምን መደረግ አለበት በሚል ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ውይይት ማድረጉን አበረታች ሲሉ ተናግረው፣ መድረኩ ቀጣይነት ሊኖረው እንደሚገባም እንደሆነ አስታውቀዋል።

ከ17 ሺ የሚልቁ አባላት ያሉት የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት "የብድር አቅርቦት ፋይዳ ለቢዝነስ" በሚል መሪ ሃሳብ ከሚመለከታቸው አካላትጋር ባደረገው በዚህ ውይይትም የብድር አቅርቦት ሚናን፤ የግሉ ዘርፍ የብድር ተጠቃሚነትንና የሚታዩ ችግሮችን በሚመለከት እንዲሁም የብድር አሰጣጥ ተደራሽነትና በንግድ ባንኮች የብድር አሰጣጥ ዙሪያ ያጋጠሙ ችግሮችና መፍትሔዎቻቸው የሚሉት ጉዳዮች ተነስተዋል።

የብሔራዊ ባንኩ ጽሑፍ አቅራቢ አቶ በለጠ አፎላ እንዳሉት፤ ብሔራዊ ባንክ በአዋጅ ከተሰጡት ተግባራት መካከል ለፋይናንስ ተቋማት ፈቃድ መስጠትና ተቋማቱን መቆጣጠር አንዱ ሥራው ነው።በመሆኑም ከብድር ፖሊሲ ጋር በተያያዘ ትልቅ ትኩረት ሰጥቶ ይሰራል።ለዚህም ባንኮች ከብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ማግኘት የሚችሉት የብድር ፖሊሲ ማውጣት ሲችሉ እንደሆነና ሕጉ አስገዳጅ ሕግ እንደሆነ ነው የተናገሩት፡፡

የባንክ ቦርድ ዳይሬክተሮች ዋና ኃላፊነት የብድር ፖሊሲን ማውጣት፣ ማሻሻልና ተቀባይነታቸው የተሟላ መሆኑን ማረጋገጥ ነው።ከዚህ ባሻገር የወጡ

> **በሀገሪቱ ንግድና ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ የንግድ ዘርፉ ትልቅ አስተዋጽኦ ያበረክታል።የንግዱ ዘርፍ ተወዳዳሪ እንዲሆንና ለምጣኔ ሀብታዊ እድገት አስተዋፅኦ እንዲያበረክት በጥናት የተደገፈ የብድር አቅርቦት ማመቻቸት ያስፈልጋል**

ፖሊሲዎችና ሕጎች ላይ በየጊዜው ቁጥጥርና ክትትል በማድረግ በትግበራ ሂደት አላግባብ የሚሠሩ ሥራዎች ካሉም የማረም ኃላፊነት ያለባቸው ሲሆን፤ በዚህም ለተበዳሪዎች ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠርና ማመቻቸትን ይጨምራል ነው ያሉት፡፡

ከተበዳሪዎች አንጻር ብድር ከመክፈል ጋር የተያያዙ ችግሮች ሲያጋጥሙ ተጨማሪ ብድር መጠየቅ የሚቻልበት ምቹ ሁኔታ ስለመኖሩ ያነሱት አቶ በለጠ፤ ተበዳሪው ብድሩን የሚከፍልበትን ጊዜ ከማራዘም ጀምሮ የብድር ዓይነቶችን በመቀያየር እንዲሁም ሌሎች የተለያዩ አማራጮችን መጠቀም የሚችልባቸው ምቹ ሁኔታዎች መኖራቸውም ገልጸዋል። እሳቸው እንዳሉት፤ በተለያየ ምክንያት የብድር አቅርቦት ጉዳይ በሚበላሸበት ወቅትም እንዲሁ በተሻሻለው መመሪያ መሠረት ከአምስት እስከ ስድስት ጊዜና ተጨማሪ ብድር መጠየቅና በተለያየ የአከፋፈል ሁኔታ መክፈልና ማስታመም የሚችሉበት ምቹ ሁኔታ ስለመኖሩም ጠቁመዋል፡፡

ብድር ከመስጠቱ አስቀድሞ ተበዳሪዎች በብድር አሰጣጥ ዙሪያ ስላሉ መመሪያዎችና ደንቦች በሚገባ ማወቅ አለባቸው የሚሉት አቶ በለጠ፤ መሬት ላይ ያለው እውነታ ግን ይህ አለመሆኑን ነው ያስታወቁት።አስገዳጅ መመሪያው ላይ በግልጽ የተቀመጡትን ሁሉ ተበዳሪዎች ማወቅና መረዳት ይኖርባቸዋል።ተበዳሪዎች ይህን መረዳት ሲችሉ ማንኛውንም ቅሬታ ይዘው መቅረብና ለችግሩ የተቀመጡ የተለያዩ የመፍትሔ አማራጮችን መጠቀምና ችግሮቻቸውን መፍታት ይችላሉ ሲሉ አስገንዝበዋል።

ባንኮችም ብድር ከመስጠት ጋር ተያይዞ የሚያጋጥሟቸው ችግሮች ስለመኖራቸው የጠቀሱት አቶ በለጠ፤ ደንበኞች ብድራቸውን በራሳቸው ፍላጎትና ተነሳሽነት ለመክፈል ጥረት ሲያደርጉ አይታዩም ይላሉ።ተበዳሪዎች ብድር ከመክፈል ሳይሆን ላለመክፈል የተለያዩ ምክንያቶችን እንደሚያቀርቡ ገልጸው፣ እንዲህ ዓይነት ዝንባሌዎች በተበዳሪዎች በኩል የሚስተዋሉ ባንኮችን የሚጠቅሷቸው ቁልፍ ችግሮች እንደሆኑም አብራርተዋል።

በግሉ ዘርፍ የብድር ተጠቃሚነት እና ተግዳሮቶች ላይ ጽሑፍ ያቀረቡት የዘርፉ ባለሙያና ከንግድ ምክር ቤቱ ጋር ለረጅም ጊዜ የሠሩት አቶ ጌታቸው ተክለማርያም ለሀገሪቱ የግል ዘርፍ የሚደረግ የብድር አቅርቦት ከምጣኔ አንጻር እያደገ መምጣቱን ገልጸዋል።

የፋይናንስ አቅርቦቱን ከማሻሻል አንጻር ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያለ መሆኑንም ጠቁመዋል።የሀገሪቷን ኢኮኖሚ ለማሳደግ፣ የተሻለ የሥራ ዕድል ለመፍጠርና የግሉ ዘርፍ ያለበትን ችግር ቀርፎ የተሻለ አቅም ያለው የግል ዘርፍ ለመፍጠር ውስን የሆነውን ሀብት በአግባቡ መጠቀም የግድ መሆኑን አመላክተዋል፡፡

ባለፉት ዓመታት በኢኮኖሚው ውስጥ ሁለት መሠረታዊ ለውጦች ተመዝግበዋል ያሉት አቶ ጌታቸው፣ አንደኛው ከዚህ ቀደም የመንግሥት ፕሮጀክቶች እንደሚበዙና የግሉ ዘርፍ ቁጥር የተመናመነበት ጊዜ እንደነበር አስታውሰዋል።ተገቢነት የሌለው የካፒታል ክፍፍል እንደነበረም ገልጸው፤ በወቅቱ የነበረው መንግሥትም ይህን ያምን ስለነበር ተግባራዊ ሆኗል ብለዋል።

አሁን እንደ ፖሊሲ ተሻሽሎ ለግሉ ዘርፍ የተሻለ ዕድል ሊሰጠው እንደሚገባ ታምኖበት እየተሠራ መሆኑን ጠቅሰዋል።የግሉ ዘርፍ የተሻለ ኢኮኖሚውን ማንቀሳቀስ የሚችል አቅም እንዳለው በማመን መንግሥት የተለያዩ ድጋፎችን እያደረገ በመሆኑ ይህ ትልቅ ለውጥ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

መሬት ላይ ያለውን እውነታ ስንመለከት አሁን ያለው አጠቃላይ የፋይናንስ አቅርቦት በጣም ዝቅተኛ ደረጃ ይገኛል ያሉት አቶ ጌታቸው፣ ይህን ከማሻሻል አንጻር ብዙ ሥራ ይጠበቃል ሲሉ ተናግረዋል።አጠቃላይ በሀገሪቱ ያለው የፋይናንስ አቅርቦት ዝቅተኛ ቢሆንም፣ የፋይናንስ አቅርቦት ለግሉ ዘርፍ ቀዳሚ ጉዳዩ ነው ሲሉ አስገንዝበዋል።አብዛኛው የግሉ ዘርፍ ቀዳሚ ችግር የፋይናንስ አቅርቦት እጥረት መሆኑ በጥናት መለየቱን አስረድተው፣ ይህም ከሌሎች ችግሮች በበለጠ ጎልቶ እንደሚታይ ነው ያመለከቱት።

ቀደም ሲል ያለው የብድር አቅርቦትም ቢሆን ከተማ ተኮር መሆኑን ያነሱት አቶ ጌታቸው፤ በተወሰነ መልኩ አሁን አሁን መሻሻሎች መታየታቸውን ጠቅሰዋል።ለአብነትም በተለያዩ የገጠር ከተሞች የባንክ ቅርንጫፎች መስፋፋትና መሻሻሎች እየታዩ እንደሆነ ገልጸው፣ ባጠቃላይ የመንግሥት ብድር እየቀነሰ የግሉ ዘርፍ ብድር ደግሞ እየጨመረ መምጣቱን ነው ያስረዱት።ከአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት /ከጂዲፒ/ ጋር ሲነጻጸር መሻሻሉ ብዙም እንዳልሆነ አመላክተዋል።"ከፍተኛ የሆነ የብድር ፍላጎት አለ፤ አቅርቦቱ በጣም ዝቅተኛ ነው፣ ይህም በብድር አቅርቦትና ፍላጎት መካከል ሰፊ ክፍተት ያለ ስለመሆኑ ያስማማል" ብለዋል።

ካለው ፍላጎት አንፃር አቅርቦቱ በቂ አለመሆኑን ጠቅሰው፣ ችግሩን ለመፍታት የፋይናንስ ዘርፉን ዲጂታላይዝድ ማድረግና መንግሥት መውሰድ የጀመራቸው ማሻሻያዎች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ከተደረገ ለውጥ ማምጣት ይቻላል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ሌላኛው ጽሑፍ አቅራቢ አቶ ቴዎድሮስ ኃይሉ በበኩላቸው በሀገሪቱ የንግድ ባንኮች የሚሰጠው የብድር አቅርቦት እያደገ መምጣቱን አስታውቀው፣ በተያዘው ዓመት በአንዳንድ ባንኮች ካልተሰበሰበ ብድር (ሊኩዲቲ) ጋር በተያያዘና በሌሎች ምክንያቶች አቅርቦቱ ቅናሽ ማሳየቱን ተናግረዋል። የግሉ ዘርፍ ተወዳዳሪና ለምጣኔ ሀብታዊ እድገት አስተዋጽኦ ጉልህ ሚና የሚያበረክት እንደመሆኑ ጠንካራ የንግድ ዘርፍ ለመፍጠር የብድር አቅርቦትን ማሻሻል የግድ መሆኑን አመላክተዋል።ለዚህም በመንግሥት በኩል የተለያዩ ጥረቶች እየተደረጉ እንደሆነና መሻሻሎች እንዳሉ ነው ያመላከቱት።

የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ወይዘሮ መሰንበት ሸንቁጥ፤ በበኩላቸው ምክር ቤቱ የግሉን ዘርፍ መብት ፍላጎትና ጥቅምን እንደሚያስጠብቅ ገልጸዋል።በሀገሪቱ ንግድና የኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ የበኩሉን ድርሻ እየተወጣ ያለ የግሉ ዘርፍ ድምጽ መሆኑን አመልክተው፤ ምክር ቤቱ ንግድና ኢንቨስትመንት እንዲሻሻል ከፍተኛ አስተዋጽኦ አላቸው ብሎ ከለያቸው ዘርፎች መካከል የፋይናንስ ጉዳይ ቀዳሚ እንደሆነ ጠቅሰዋል።

በአዲስ አበባ ከተማም ሆነ በሌሎች የሀገሪቱ ክፍሎች ውስጥ በተለያዩ የንግድ ሥራዎች የተሰማሩና በተለያየ የንግድ ደረጃ ያሉ አባላቱ በብድር አቅርቦት ዙሪያ ቅሬታ እንዳላቸውም ፕሬዚዳንቷ ተናግረዋል።ምክር ቤቱም የአባላቱን ቅሬታ ተቀብሎ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ውይይት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የማስተማር ሥራ ሲሰራ መቆየቱን ገልጸዋል።ችግሩ አሁንም እንዳልተፈታ ጠቅሰዋል።

ፕሬዚዳንቷ፤ በሀገሪቱ ንግድና ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ የንግድ ዘርፉ ትልቅ አስተዋጽኦ ያበረክታል።የንግዱ ዘርፍ ተወዳዳሪ እንዲሆንና ለምጣኔ ሀብታዊ እድገት አስተዋፅኦ እንዲያበረክት በጥናት የተደገፈ የብድር አቅርቦት ማመቻቸት ያስፈልጋል ይላሉ፡፡

እሳቸው እንዳሉት፤ የብድር አቅርቦቱን በአግባቡ ተደራሽ ማድረግ ከተቻለ ዜጎች በማኑፋክቸሪንግ፣ ኢንዱስትሪ፣ በግብርናና በአገልግሎት ዘርፍ በመሰማራት ለኢኮኖሚ ዕድገቱ የድርሻቸውን መወጣት ያስችላቸዋል።ይሁን እንጂ በቂ ያልሆነ የብድር አቅርቦት፣ የብድር መክፈያ ጊዜ ማጠር፣ የብድር ማስያዣ መስፈርት ግልፅ አለመሆንና፣ የብድር መክፈያ ምጣኔ ከፍተኛ መሆን ለንግድ ሥራው ትልቁ ማነቆ ሆኗል።ብድር ለማግኘትና ለማስፈቀድ የሚወስደው ጊዜ ረዥም መሆንና የብድር ዓይነቶች አለመስፋት ተጨማሪ ችግሮች ናቸው፡፡

ይሁንና ምክር ቤቱ የግሉን ዘርፍ በማጠናከር በሀገሪቱ ንግድና ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ የበኩሉን ሚና እየተወጣ እንደሆነ ገልጸው፤ ምክር ቤቱ በእነዚህ ችግሮች ዙሪያ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመምከር የመፍትሔ ሃሳብ ለመንግሥት ለማቅረብ እየሠራ መሆኑን ተናግረዋል። እነዚህን ችግሮች በመፍታት በባንኮችና ማይክሮ ፋይናንሶች ፖሊሲና መመሪያን መሠረት ያደረገ የብድር አቅርቦት እንዲፈጠር መንግሥት በትኩረት መሥራት እንዳለበትም አመላክተዋል።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## ነውር ነው!

**ሙሉጌታ ብርሃኑ**

ነውር የምንላቸው የአደባባይ ህጸጾቻችን እንደ ሰልፈኛና ታንከኛ ወታደር ጦር አንግበው ተጠግጥገዋልና፤ ዘንድሮ እህ! ከተባለ የማይሰማ፤ ዞር ዞር ብለው ካዩ ከአይን አልፎ የማያዞር ነገር የለም። "ነውር ነው!" ብንልም ጉዶች እየበዙ መጣያ ጉድጓዶቹም ሞሉ። በጨለማ እያደፈጠ በአፍ ጢም የሚደፋው አንደኛው ጉድጓድም፤ የትዳር ዳቦ የተቆረሰበት ትሪ፤ ላይወርድ ከሚሰቀልበት የፍቺ ቤት ውስጥ ነው።

ነገርየው ሲጀማምር አካባቢ የምንናገረው፤ በዓሉ አሉ...በወሬ ወሬ ቢሆንም አሁን ግን ሁላችንም ለዚህ አዲስ የምንሆን አይመስለኝም። ድሮ ድሮ ድል ያለ ድግስ ሲባል ለሠርግ ነበር። ድል የምትለዋን ቃል ስንሰማም ወዲያው በአዕምሯችን የሚከሰትልን ምናባዊ ስዕል፤ ሠርግና ሠርግ ቤት ነበር። ወዳጄ፤ አሁንም እንዲህ ብቻ ከታየህ፤ የምናብህ ሰዓሊ ተሳስቶ እያሳሳተህ ነው። ለምን በለኝና ልንገርህ... ምክንያቱም ዘንድሮ ላይ ድል ካለው የሠርግ ድግስ የላቀ ድል ያለ የፍቺ ድግስ እየተደገሰ ስለሆነ ነው። ካላመንከኝ ከአንዱ ቅንጡ ሆቴል ጎራ በልና ዘልቆ የመግባቱን ዕድል ካገኘህ አንደኛውን አስተናጋጅ በጨዋታ አደንዝዘህ፤ ወገቡ እስኪንቀጠቀጥ ጎንበስ ቀና እያለ ያስተናገደባቸው የፍቺ ዝግጅቶች ስንት እንደሆኑ ጠይቀው ይነግርሃል።

እንዲያውም ቀለል ያለውን ልጠቁምህ፤ ከአንደኛው የፎቶግራፍ ስቱዲዮ ግባና፤ እስካዛሬ በስንት የፍቺ ዝግጅቶች ላይ ተገኝቶ፤ ካሜራውን አንቀጫቅጮ እንደወጣ ብትጠይቀው እሱ ይነግርሃል። ይህ ሁሉ የሚያደክምህ ከሆነ ግን ስልክህን ከፍተህ እነ ቲክቶክና ዩቲዩብ መንደር ዝለቅ፤ እንዲያውም እሷን መርጬልሃለሁ። ቀድሞ በሠርግ ላይ እንደለመድነው ሁሉ "ከነባለቤትዎ.." የሚል የጥሪ ካርድ ቢደርስህስ ግን ምን ይሆን የሚሰማህ? ይልቅ እንዳይሆን ብቻ ጸልይ፡፡

ወትሮ ፍቺ ስነልቦናዊ ጫናን ያስከትላል የሚሉት የስነ አዕምሮ ጠበብት አሁን አሁን ግን ብሂላቸውን ለመቀየር ሳይገደዱ አልቀረም። ነገሩ በተቃራኒው አኩሪ ጀብዱ እየሆነ ስለመምጣቱ ከማንም በላይ የማህበራዊ ሚዲያዎቻችን ይነግሩናል። "የዛሬ ዓመት፤ የማሙሽ አባት/እናት፤...ለክርስትናው እንመጣለን ገና.." ሲሉ አባሯውን ያስጨሱ ሚዜና አጃቢዎች "ጽድቁ ቀርቶ በቅጡ በኮነነኝ" እንዲሉ፤ የዛሬ ዓመት የፍቺው ድግስ ላይ የሚገናኙ ቀላል አይደሉም። በሠርጉ ዕለት ቢራ እየከፈቱ ተራጭተው፤ አበባው ከላይ ከታች ተበትኖ በዓመቱ የሰማንያውን ወረቀት እየቀደዱ በሂሊኮፕተር የተበተነ ያህል፤ ፍርድ ቤቱን አልፎ ከየአዳራሹ ... ምን አይነቱ የአዕምሮ ልህቀት ይሆን? ጽድቅ ካለ ኩነኔ፤ ህይወት ካለ ሞት፤ ትዳር ካለም ፍቺ ሁሌም የሰው ልጆች ባሉበት ሁሉ የሚኖር ነገር ነው።

ይህ አፈንጋጭነት ነውና መሆን የለበትም ስንልም ፍቺውን ብቻ ሳይሆን ከፍቺው በስተጀርባ ያሉትን የህጸጽ አጀቦችንም ነው። ዘንድሮ ላይ ከሚያገባው ይልቅ የሚፋታው፤ ከሠርጉም ፍቺው በልጧል፤ የሚልን መረጃ በውሸት ለመንቀፍ የሚያዳግት ሆኗል። ካለን የጠነከረ ባህልና ሃይማኖት እንዲሁም የማህበረሰባችን የአኗኗር ዘዬ የተነሳ፤ ፍቺም ሆነ ስለፍቺ ጎልቶ የማይታይባት የኛ ሀገር ነበረች። "ከኋላ የመጣ አይን አወጣ" አይነት ሆኖ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ብቻ የሚታዩ ነገሮች የአፍሪካ ቀንድ ላይ ብቻም ሳይሆን የፍቺው ቀንድ ላይም ሊያስቀምጣት ነው። የፍርድ ቤቶቹ የፍቺ መዝገብም አልበረከት ብሏል። ለዛሬው ይህን እንተወውና ከፍቺዎቻችን በስተጀርባ ያለውን ተንጠራርተን ለማየት እንሞክር።

ለምን እና በምን ምክንያት ነው የምንፋታው ከማለት ይልቅ እንዴትና በምን መልኩ ነው የምንፋታው፤ የሚለው አይሎ ከያኔው ሠርግ በላይ አስጨናቂ ሆኗል። ሰው እንዴት ድል ያለ የፍቺ ድግስ ፈችሮ፤ ምርጥ ፈቺና ተፋቺ ለመሆን ይጥራል? ነውር አይደለም? በዚህ ፍቺ ውስጥ፤ ሰብአዊ ስብዕናችንን፤ ባህልና ሥርዓታችንን፤ ሃይማኖትና እምነታችን...አስቀድመን ወደ ገደል የምናስገባቸው ነገሮች ናቸው።

ዛሬ እንደ መብት ያየነው ነገር ውጤቱ ከባህል ማፈንገጥ ብቻ ሆኖ አይቀርም፤ የኋላ ኋላ እንደ እባብ በደረታቸው እየተሳቡ የሚመዘዙ ጉዶች አሉት። ምን ችግር አለው ያልናቸውም፤ መልሰው ከማንወጣው ችግር ደፍቀውናል። እዚህ ጋር የማንዘለውን ሃሳብ ላስፍር። ፍቺ ከነጻነት ጋር የተያያዘበት መንገድ ግለሰባዊና የእይታ ጉዳይ ብቻ እንዳይመስለን። ከፍቺ በስተጀርባ ከግለሰብና ከሀገር የላቀ ግዙፍ እጅ ያለበት ነው። ይህ እንደነውር የተገለጠው ጉዳይ ጀርባው ከነውርነትም ያለፈ ሌላ ጉድ አለው። እኛ እንደ ግለሰብ፤ ለመፋታታችንም ሆነ ለመደገሳችን አንዳንዶች የራሳችን የውስጣዊ ምክንያት ሊኖረን ይችላል፤ ነገር ግን ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ እያየለ የመጣው የፍቺ ሁኔታና ድል ያለው ድግስ፤ግብሩ በዘፈቀደ ቢመስልም፤ አጀማመሩ ግን በምክንያትና በዓላማ ነው፡፡

የፍቺው ድግስ ከትዳር ባርነት አምልጦ፤ ወደ ነጻነት ደሴት የመግቢያ ማብሰሪያው ነው። በፍቺ ጀልባ ተሳፍረን ወደ ደሴቱ እንድንገባ እየሰሩ ያሉ ስውር ደላሎች እንዳሉ ስንቶቻችን እናውቃለን? የሚሰዱን ግን በበረሃ ሳይሆን ከደሴቱ በስተጀርባ ወዳለው በረሃ ነው።

አሁንም በድጋሚ ካላመንክ፤ ልበልና መከረኛውን የማህበራዊ ሚዲያ ተመልከትን ልድገም፤ ብዙ የፀረ ትዳርና የፍቺ አብዮት አቀንቃኝ ሰባኪዎችን ታገኛለህ። ከእነርሱ በስተጀርባ ያለውንም ዓለም ከተመለከትክ፤ መንገዱ በቀጥታ ወደ ምስጢራዊው ዓለም ማህበረሰብ ይወስድሃል። በአንድ ደሴት ሁለት ንጉሥ አይኖርምና፤በተመሳሳይ ጾታ የሚሰራውን ዓለም ለመገንባት፤ በተቃራኒ ጾታ የተጋቡትን ማፍረስ ግድ ይላቸዋል። አሁን የምንለውን ጉዳይ በዓለም ዙሪያ እንዲስፋፋ በማድረግ ወደዚህ የነጻነት ወደሚሉት ዓለም ማጋዝ ጀምረዋል። ፍቺው መበርከቱ በዋዛና በአጋጣሚ አይደለም። በእንቅስቃሴያቸው ውስጥ ያላገቡትን እንዳያገቡ፤ ያገቡትንም እንዲወጡ ማድረግ ቁልፍ ነገር ነው። በእነርሱ እሳቤ ጎጆ ማፍረስ፤ ከትዳር መፋታት ሳይሆን ከእስር መፈታት ነው። እኛ ምንም እንበለው ምን፤ በድግሱ ጅምር ዓላማ ውስጥ ግን፤ የዚህ ትግል ድልና የድል ማብሰሪያ መስዋዕት እንዳለበት ግን እንወቅ። ይህን በዚሁ እንቋጨውና ሌላ አንድ ነገር ልመርቅላችሁ፡፡

ከወራት በፊት የወዳጄ ወዳጅ፤ የገጠመውን ነገር ወዳጄ አጫወተኝ። እናም፤ የወዳጄ ወዳጅ የሩቅ ዘመዱ ሞቱና ወደለቅሶው እንደሚሄድ ለወዳጄ ነገረው። በማግስቱም አግኝቶ፤ ታዲያስ ለቅሶውን ደርሰህ መጣህ፤ ብሎ ቢጠይቀው፤ "አዎን ነገር ግን የደረስኩት ሠርጉ ላይ ነው" አለው። ለቅሶ ሄዶ ከለቅሶ ቤት ደግሞ የምን ሠርግ ነው፤ በማለት ቀልዱን ነው ብሎ ቢያስብም ከፊቱ ላይ ግን ምንም የቀልድ ለዛ አይታይበትም። ይልቅስ ቃላቱም የንዴት ስላቅና አሽሙር ናቸው። ግራ መጋባቱን ግራ በተጋቡ ቃላት እንዴት ሲል ጠየቀው። ልጁም እንዲህ አለው፤ ሰውየው ስለመሞቱና ለቅሶ ቤት ስለመሆኑ ያመንኩት ከተንጣለለው ግቢና ከተንፈላሰሰው ህንጻ ወገብ ላይ የተንጠለጠለውን የሟችን ፎቶ የያዘ የሸራ ላይ ጽሁፍና "ጋሼ እንወድሃለን" የሚለውን መፈክር አይቼ ነው። የምመለከታቸውና የሚሆኑ ነገሮች በሙሉ ከሞት የተነሳ እንጂ ወደ ሞት ሄዶ የተለያቸው አይመስልም። የሰውየው ልጅ ያገባች ጊዜ ሠርጉን በልተን ሀገር ምድሩ ጉድ! ብሎ ነበር። ነገር ግን ይህኛው የባሰ ነው። ሲል የታዘባቸውን ጉዳዮች እንደነገረው አጫወተኝ። በጊዜው በገጠመኙ ብንሳሳቅም፤ በባህልና በሰብአዊነት ማንነት ካየነው ግን በጥርስ አያድርስ የሚያስብል ነው። ጉዱን ባየ ሟች...እዚህ ጋር ግን ምንም ለማለት አልወድምና የነብስ ይማር ሥርዓታችንን እራሱኑ ነብስ ይማር ብለን ሳንቀብረው በፊት፤ እናንተው አይታችሁ ባህልን ፍረዷት፡፡

# ዓለም አቀፍ



## በአውስትራሊያ ሲድኒ በሚገኝ "ቸርች' ውስጥ በርካቶች በስለት ተወጉ

በአውስትራሊያ ሲድኒ ከተማ በሚገኝ 'ቸርች' ውስጥ በርካቶች በስለት ተወጉ። አውስትራሊያ ሲድኒ ከተማ ዳርቻ በሚገኝ 'ቸርች' ውስጥ በተፈጸመ በስለት የመወጋት አደጋ በርካቶች መቁሰላቸውን ፖሊስ አስታወቀ።

በማህበራዊ ሚዲያ የተለቀቀው ቪዲዮ ቢለዋ የያዘው ግለሰብ መድረክ ላይ የነበረውን አገልጋይ ጎትቶ ሲወጋው ይታያል። ፖሊስ ይህን ጥቃት አድራሽ መያዙን እና ለምርመራ ተባባሪ መሆኑን የፖሊስ ቃል አቀባይን ጠቅሶ ሮይተርስ ዘግቧል። ይህ ጥቃት ከሴንትራል ቢዝነስ ዲስትሪክት በስተምዕራብ በኩል በምትገኘው ዌክሌይ ላይ የተፈጸመውን ጥቃት ተከትሎ የተፈጸመ ነው።

በሲድኒ በሚገኝ የገበያ አዳራሽ ውስጥ ስድስት ሰዎች በቢለዋ ተወግተው ከተገደሉ በኋላ በሦስት ቀናት ውስጥ ለሁለተኛ ጊዜ የተፈጸመ ጥቃት ነው ተብሏል። ትናንት አደጋ የተከሰተው ዌክሌይ ውስጥ የሚገኘው 'ክሪስት ዘ ጉድ ሸፐርድ ቸርች' አገልግሎት እየሰጠ ባለበት ወቅት ሲሆን፤ ፖሊስ በቦታው የተሰበሰበውን ሕዝብ ለመቆጣጠር እስካሁን በቦታው እንደሚገኝ ተዘግቧል።

በሰዎች ላይ የደረሰው ጉዳት ለህይወት አስጊ አለመሆኑን እና ህክምና እየተደረገላቸው መሆኑን ፖሊስ ገልጿል። በአደጋው የቸርቹ መሪ እና በርካታ ምዕመናን ጉዳት ደርሶባቸዋል። በማህበራዊ ሚዲያ የተለቀቀው ቪዲዮ ቢለዋ የያዘው ግለሰብ መድረክ ላይ የነበረውን አገልጋይ ጎትቶ ሲወጋው ይታያል ሲል አል ዐይን ዘግቧል።

## ኢራን በእስራኤል ላይ ጥቃት ከሰነዘረች በኋላ የዓለም ነዳጅ እና ወርቅ ዋጋ ቀነሰ



ባለፈው ሳምንት ማብቂያ ኢራን እስራኤል ላይ የጥቃት እርምጃ ከወሰደች በኋላ ከሰኞ ጀምሮ የዓለም የነዳጅ ዋጋ ላይ ቅናሽ ታይቷል። የዓለም የነዳጅ ዋጋ ማነጻጸሪያ የሆነው የድፍድፍ ነደጅ ዋጋ እያሽቆለቆለ ሲሆን በበርሜል ወደ 90 ዶላር እየተጠጋ ይገኛል።

ተንታኞች ኢራን እስራኤል ላይ ያደረሰችው ጥቃት ዓለም አቀፍ የገበያ ሰንሰለት ላይ የሚያደርሰው ተጽዕኖ ወደፊት የሚታይ ይሆናል ብለዋል። የዓለም የነዳጅ ዋጋ መለዋወጥ በርካታ ሀገራት ለምርት የሚመረኮዟቸውን የቤንዚል እና ናፍጣ ዋጋን ተቀያያሪ በማድረግ የዓለም ገበያ እንዳይረጋጋ ያደርጋል። ባለፉት ጥቂት ዓመታት በዓለም ዙሪያ ለታየው የምርቶች ዋጋ ማሻቀብ ዋነኛው ምክንያት የነዳጅ ዋጋ ማሻቀብ ነው።

በአውሮፓውያኑ 2022 የሩስያ ዩክሬንን ጦርነት ተከትሎ የአንድ በርሜል ነዳጅ ዋጋ ወደ 120 ዶላር ጨምሯል። የዚህም ምክንያት ሩስያ ላይ ምዕራባውያን የጣሉት ማዕቀብ ነው።ይህ እርምጃ የነዳጅ ዋጋ ብቻ ሳይሆን በዓለም የምርቶች ዋጋ ላይ ከፍተኛ ጭማሪ እንዲታይ ሰበብ ሆኗል።

ታዲያ እስራኤል አሁን የምትሰጠው አጸፋ የዓለም የነዳጅ ዋጋን ለመወሰን ወሳኙ እንደሆነ ታምኗል። የእስራኤሉ መከላከያ ሚኒስትር ዮአቭ ጋላንት ከኢራን ጋር የገባነው ፍጥጫ አላበቃለትም ብለዋል።ሚኒስትሩ ይህንን ያሉት ኢራን ባለፈው ቅዳሜ እስራኤል ላይ ለፈጸመችው ጥቃት ምላሽ ለመስጠት እየተዘጋጁ ነው።

ባለፈው ሳምንት ማብቂያ ላይ የድፍድፍ ነዳጅ ዋጋ በበርሜል 92 ነጥብ 18 ዶላር የነበረ ሲሆን፤ ይህም ከጥቅምት ወር ወዲህ የተመዘገበው ከፍተኛው ዋጋ ነበር። ሆኖም ትናንት ሰኞ ወደ 89 ነጥብ 50 ዶላር ወርዷል። ሌላው በዓለም ገበያ አስተማማኙ ኢንቨስትመንት እንደሆነ የሚቆጠረው የወርቅ ዋጋም ቀንሷል።

የወርቅ ገበያ ባለፈው ዓርብ በወቄት 2 ሺህ 431 የነበረ ሲሆን፤ ይህም ከፍተኛው የወርቅ ዋጋ ሆኖ ተመዝግቧል። አሁን ዋጋው በወቄት ወደ 2 ሺህ 332 ነጥብ 9 ዶላር ቀንሷል። ኢራን የዓለም ሰባተኛዋ ከፍተኛ ነዳጅ አምራች ሀገራት ስትሆን፤ ሦስተኛዋ ትልቁ የነዳጅ ላኪዎች ኅብረት ወይም ኦፔክ ሀገራት አምራች ነች።

ታዲያ ተንኞች የዓለም የነዳጅ ዋጋን የሚወስነው በግጭቱ ሆርሙዝ ሰርጥ ምን ያህል ተጽዕኖ ውስጥ ይወድቃል የሚለው እንደሆነ ይናገራሉ። ሆርሙዝ ሰርጥ ነዳጅ የሚመላስበት መስመር ነው። በኦማን እና ኢራን መካከል ያለው ይህ ሰርጥ የዓለም እስከ 20 በመቶ የሚደርሰው ነዳጅ የሚጓጓዝበት ነው። የኦፔክ አባላት የሆኑት ሳውዲ አረቢያ፣ ኢራን፣ ዩኤኢ ኩዌት እና ኢራቅ ይህንን መስመር ተጠቅመው ነዳጅ ይልካሉ።

ባለፈው ቅዳሜ ኢራን በዚህ ሰርጥ ሲተላለፍ የነበረ እና ከእስራኤል ጋር ግንኙነት ያለውን መርከብ ይዛለች። በሰርጡ ይህንን አይነት ውዝግብ ከቀጠለ እና ጉዞዎች የሚስተጓጎሉ ከሆነ የዓለም የነዳጅ ዋጋ በከፍተኛ ሁኔታ ሊያናጋው እንደሚችል ተሰግቷል ሲል ቢቢሲ ዘግቧል።

# ነፃ ሃሳብ

# ስለ ሕዝባችን

## ሰላም ቀድመን ከራሳችን ሰላም ጋር እርቅ እናድርግ!

ታሪኩ ዘለቀ

ሰላም የሁሉ ነገር መሠረት ነው ሲባል ከጦርነት ጭንቀት ማሳረፉ ወይም ሞትና ውድመት አለመኖሩ ብቻ ሳይሆን ጦርነትን ተከትለው የሚመጡ ብዙ ተያያዥ ችግሮች ስላሉት ጭምር ነው።በጦርነት ውስጥ ሆኖ ያደገ ሀገር የትም አይገኝም። የሩሲያና ዩክሬን ጦርነት ለአንዳንድ ሀገራት ሥርግና ምላሽ እንደሆነላቸው ከዳር ሆነው እሳቱ እንዳይጠፋ ለሚያራግብ እንጂ ለሁለቱም በዘመናት ለማይወጡበት አዘቅት እየከተታቸው ነው።በእስራኤል ሀማስ ጦርነት እየወደመች ያለችው ጋዛ ትሁን እንጂ እስራኤል በፖለቲካዋ፣ በኢኮኖሚዋ፣ በዲፕሎማሲዋ፣ በሕዝቧ ሥነ ልቡናም ዋጋ እየከፈለች ነው፡፡

የጦርነት አስከፊነት በጦርነት ወቅት የሚከሰተው ሞት፣ ውድመት፣ መፈናቀል፣ ስደትና ሌሎች ችግሮች ብቻ ሳይሆኑ ከዚያ በኋላ መልሶ የነበረን ሥነ ልቡናን ማግኘት እጅግ አስቸጋሪ ነው።ያለዚህ ሥነ ልቡና ደግሞ ሰው ተስፋ ወደ መቁረጥ ይገባል።በሀገሩ ተስፋ የቆረጠ ደግሞ ወይ ይሰደዳል፣ ባስ ሲልም ወደ አጥፊነት ይቀየራል።

ይህ በብዙ ሀገራት ውስጥ የተከሰተ ነው።ጥናቶች እንደሚያመላክቱት ኢራቃዊያንና አፍጋኒስታናዊያን ምንም በሌለበት የሚበረግጉ፣ ያልተረጋጉ ማህበራዊ ቀውስ ያጋጠማቸው ሆነዋል።ኢራቅ በጦርነቱ በቀጥታ ከደረሰባት ውድመት ይልቅ ከጦርነቱ በኋላ ራሷን ለማረጋጋት ያወጣችው ወጪ በብዙ እጥፍ ይልቃል።

ሊባኖስም እንዲሁ ከእርስ በርስ ውጊያ ከተላቀቀች አስር ዓመታት ብታስቆጥርም አሁንም ግን በሕዝቡ ውስጥ ልዩነቱ፣ ፍርሃቱ፣ ጥርጣሬው ወይም ትራወማው አለቀቀም።ትራሱ ስር መሳሪያ የሚያስቀምጥ ሊባኖሳዊ አሁንም ብዙ ነው።የሰላምን ዋጋ ሰላምን ያጡት ያውቁታል።

ከጦርነት ታሪካችን ከአስከፊው ኪሳራችን መማር ባለመቻል በሕዝብ ደህንነት በኩልም ሆነ በሀገር እድገት ከሌሎች በታች አድርጎናል።አሁንም ድረስ ግጭት እና አለመግባባት የሰላም እጦት ሀገርና ሕዝብን በብዙ እየጎዳ ነው።ግጭትና አለመግባባት ሲኖር የሰው ሕይወት ይጠፋል ሀብትም ባልተገባ ቦታ ይውላል።

ከአክሱም ዘመነ መንግሥት ጊዜ ጀምሮ አሁን እስካለንበት ጊዜ ድረስ ያለን የጦርነት ታሪክ ነው።ሌሎች ሀገራት ከጦርነት ታሪካቸው በዘለለ ስለሕዳሴአቸው /ሬኔሳንስ/፣ ስለትራንስፎርሜሽናቸው፣ ስለኢንድስትሪ አብዮታቸው ሊያስተምሩ ይችላሉ።

እኛ ያለን ታሪክ የጦርነት ታሪክ ብቻ ነው ማለት ይቻላል።ከሱም ቢሆን በአግባቡ መማር አልቻልንም።ከጦርነት ወደ ጦርነት አሁንም እንደጋግመዋለን።ይህ መሆኑ ከፍተኛ ውድቀት አስከትሎብናል።አሁን ኢትዮጵያ ላለችበት የኢኮኖሚም ሆነ የፖለቲካ ዝቅጠት ዋነኛ ምክንያት ሆኗል፡፡

ችግርን በሰላማዊ አካሄድ ለመፍታት ዝግጁነት መጉደሉ ለቀውስና ኪሳራ ዳርጓል።ከታሪክ መረዳት እንደሚቻለው የአንደኛውና የሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ የጦርነትን አስከፊነት ተረድተው ሰላምን አምጥተው ሀገራት ራሳቸውን አሳድገዋል።ለዚህም ለሰላም የነበራቸው ቁርጠኝነት ወሳኝ ነበር።ትናንሽ የሚባሉ የአውሮፓ ሀገራት ሳይቀሩ ለሰላም በነበራቸው ቁርጠኝነት ከግጭት ወጥተው ትልልቅ የሚባሉ የአፍሪካ ሀገራትን እየረዱ ይገኛሉ፡፡

ጦርነት አዲሳችን ባይሆንም ሞት እንደማይለመድ እንግዳ እንደሆነ ሁሉ በየሰዓቱ እንኳን ቢከሰት በየሰዓቱ የሚያስደነግጠን፣ የሚያስለቅሰን ነው። ጦርነትም በፍፁም የማይለመድ የሁሉ ጠላት ነው።ጦርነት ጠላትነቱ ለሰላም ብቻ ሳይሆን ኢኮኖሚን እሳት እንደገባ ቅቤ የሚያቀልጥ፣ ፍቅርን እንደሳይቤሪያ በረዶ የሚያቀዘቅዝ ፣ መተማመንን እንደ ጎርፍ የሚሸረሽር የሁሉ ነገር ፀር ነው።

> **ኢትዮጵያ ውስጥ አሁን እየተነሳ ያለው ጥያቄ ትክክል ሊሆንም ላይሆንም ይችላል።ይህንን የሚወስነው ሕዝብ ነው።ጥያቄዎች የምንጠይቅበት መንገድ ከመገዳደል በሃሳብ ወደ መገዳደርና በሰላማዊ የውይይት መድረክ መሆን አለበት።እንደ ሀገር ከሰላም ጋር ተያይዞ ችግር ቢኖርም ለችግራችን በአንድነት እልባት መስጠት ያስፈልጋል።ለሰላም መነጋገር መደማመጥ፣ በጠረጴዛ ዙሪያ ቁጭ ብሎ ማውራት ወሳኝ ነው።ከዚህ ውጭ ስለ ዘላቂ ሰላም ማውራት አይቻልም**

በአንድ ወቅት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ዶ/ር እንደተናገሩት፤ “የሕዝቡ ጥያቄ ግልፅ ነው።ሕዝቡ ሰላም፣ ዴሞክራሲ ይፈልጋል፤ ሁሉ ጉዳይ በውይይት እንዲፈታ፣ ልማት እንዲለማ፤ ድህነት እንዲቀንስ፤ ኢትዮጵያ ከችግር እንድትገላገል ይፈልጋል፤ ዴሞክራሲና ተቋማት እንዲገነቡ ይፈልጋል።ለምን ቢባል ሕዝብ ማለት የቀጣይነት ምልክት በመሆኑ ነው።ልጆች ያሉት ለልጆቹ የተሻለ ሀገር ይፈልጋል፡፡”

ርግጥ ነው ሕዝቡ ሰላምን አብዝቶ ይፈልጋል።ለመኖሩ የሰላም መኖር ቀዳሚ ጥያቄው ነው።የሰላም መኖር ለሕዝብ መኖር፣ መበልጸግ ብሎም መከበር ዋስትና ነው።ሰላም ዘርቶ ለመቃም፣ ወልዶ ለመሳም፣ ወጥቶ ለመግባት ሆነ ሰርቶ ለመለወጥ አስፈላጊነቱ ሳይታለም የተፈታ ነው።ለዚህም ነው ስለ ሰላም ዋጋ ከፍተኛነት ሁሌም የሚነገረው።

ጦርነት የሕይወት ዋጋን ያለስሰት ያስከፍላል።ሀገርን የኋሊት ያስጉዛል።ልክ እንደእኛ የጦርነት ጠባሳው ያልሻረለት ሕዝብ ደግሞ እውነታው የተደበቀ አይደለም።መንግስት ለሰላም ያለውን ቁርጠኝነት ትላንት ፕሪቶሪያም ሆነ ዳሬሰላም ላይ በመገኘት አሳይቷል።በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች የሚገኙ ግጭቶችን በሰላም እንዲፈቱም አበክሮ እየሰራ ነው።

ደስታን ማጣጣም፤ ሀዘንንም መካፈል የሚቻለው ሀገር ሰላም ሕዝብም ጤና ሲሆን ነው።የሰላምን አየር መማግ ለናፈቀ፣ የግጭትን ማክተም ለሻተ፣ ስቃይና እንግልት በቃኝ ላለ ሕዝብ ይህ ግልፅ ነው።የትላንት ስህተታችን እንዳይደገም በእጃችን ያለው አንፃራዊ ሰላም እንዳይጠፋ ከሕዝብ እስከ መንግሥት ባለድርሻዎች ድረስ የበኩላቸውን መወጣት አለባቸው።

ኢትዮጵያ የሰነበቱ የፖለቲካ ጥፋቶቿ በጦርነት አዙሪት ውስጥ እንድትሰነብት አድርገዋታል።ከዚህ አዙሪት ለመውጣት በመንግሥት የተጀመሩ ተስፋ ሰጪ እንቅስቃሴዎች መቀጠል እንዳለባቸው ሁሉ በተለያዩ አካባቢዎች ለሕዝብ ደህንነት ስጋት የሆኑ እንቅስቃሴዎች ላይ የሕግ ማስከበር ርምጃው ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል።

የተለያዩ ሃሳቦች ያሏቸው አካላት፣ የሕዝብ ጥያቄ ነው የሚሉት ጉዳይ ካለም አሁን ያለውን ትልቁን እድል ብሔራዊ የምክክር ኮሚሽን በሚያደርገው እንቅስቃሴ ጎን በመቆም ሥርዓት በጠበቀ መልኩ ችግሮቻቸውን በፍርድ ለመፍታት እራሳቸውን ማዘጋጀት ይጠበቅባቸዋል።

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በቅርቡ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሕዝብ እንደራሴዎች ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች ምላሽና ማብራሪያ በሰጡበት ወቅት መንግሥት ለሰላማዊ ውይይት ሁሌም በሩ ክፍት ነው ማለታቸው ይታወሳል።ታጥቀው በየጫካው የሚንቀሳቀሱ አካላትም ወደ ሰላም አማራጭ እንዲመጡ ጥሪ አቅርበዋል።

የሀገርን ሰላምና ደህንነት ለማስጠበቅ እፈልጋለሁ የሚልና ኃላፊነት የሚሰማው የትኛውም አካል የልዩነት ሃሳቡን በሰላማዊ መንገድ ለማቅረብ በመፍቀድ ሀገርን የማስቀጠል ኃላፊነቱን መወጣት ይገባዋል።

የነገ ብሩህ ግቧን አልማ እየተንቀሳቀሰች ባለችው ሀገራችን የሰላም መደፍረሶች ይስተዋላሉ።መንግሥት በቀዳሚነት ሰላማዊ አማራጮችን ቀዳሚ አማራጭ አድርጎ ቢውስድም፤ የሀገርን ህልውና ከማስቀጠል አኳያ በመንግሥት በኩል የሚወሰዱ የሕግ ማስከበር ርምጃዎች ሀገርን የመታደግ ሕጋዊ አካሄድ ናቸው።

በየትኛውም ጉዳይ ላይ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የሚፈልገውን ጥያቄዎች ማንሳት ይችላል።ጥያቄዎች የሀገርን ሰላምና ደህንነት፤ የሕዝቦችን ሕገ መንግሥታዊ መብቶች የማይፈታተን ሊሆን ይገባል። ዓለም አሁን ያለበት የፖለቲካ ሁኔታ ውስጥ ያለው እያንዳንዱ ጥያቄ ተመልሶለት አይደለም፤ ጥያቄዎች የሚጠየቁበትና የሚመለሱባቸው መንገዶች ዘመኑን የሚዋጅ በመሆኑ ነው፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ አሁን እየተነሳ ያለው ጥያቄ ትክክል ሊሆንም ላይሆንም ይችላል።ይህንን የሚወስነው ሕዝብ ነው።ጥያቄዎች የምንጠይቅበት መንገድ ከመገዳደል በሃሳብ ወደ መገዳደርና በሰላማዊ የውይይት መድረክ መሆን አለበት።እንደ ሀገር ከሰላም ጋር ተያይዞ ችግር ቢኖርም ለችግራችን በአንድነት እልባት መስጠት ያስፈልጋል።ለሰላም መነጋገር መደማመጥ፣ በጠረጴዛ ዙሪያ ቁጭ ብሎ ማውራት ወሳኝ ነው።ከዚህ ውጭ ስለ ዘላቂ ሰላም ማውራት አይቻልም።

ጥያቄዎች አልተመለሱም በሚል አላግባብ በሆኑ ስሜት ተኮር አካሄዶችና ተገቢ ያልሆኑ የትጥቅ ትግል መንገዶችን መከተል ከውጭ ለሚመጣ ጠላት ተጋላጭ ስለሚያደርገን ጥንቃቄ ያሻዋል።የውስጡ ልዩነት በጎረቤትና በሌላው ዓለም ለሚገኙ የሀገራችን ጠላቶች መግቢያ ቀዳዳ ይከፍታል።እንደመልካም አጋጠሚም ይጠቀሙበታል።

ባለመግባባት በምንሄድበት የጦርነት መንገድ፤ የሚሞተው ሰው ነው፤ የሚወድመው ንብረት ነው።ጦርነት የምንጨምረው ምንም ነገር የለም። ተጨማሪ ጣጣ ይዞብን ይመጣል።ኢትዮጵያ በአፍሪካ ቀንድ አስፈላጊ እንደሆነች ሁሉ ጦርነት በብዙ መልኩ ብሔራዊ ጥቅማችንን ይጎዳል።

ኢትዮጵያን ደካማ እና እንዳትረጋጋ በማድረግ በቋሚነት ግጭት ውስጥ እንድትኖር ማድረግ አለብን ብለው፣ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ቀርፀው የተቀመጡ፣ በገንዘብ፣ በመሳሪያ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚካሄደውን ጦርነት የሚደግፉ ወይም ስፖንሰር የሚያደርጉ አካላት አሉ።በኢትዮጵያ ውስጥ ጦርነት እንዲኖር መሥራት የሀገራችንን ታሪካዊ ጠላቶች መሰሪ አካሄድ መደገፍ ነው።ሌሎች ጣልቃ ገብነቶችንም ያስፋፋል፡፡

በየትኛውም የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ለሚነሱ ጥያቄዎች ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ ሰላምን የሚሻውን ሕዝብ ማድመጥ ነው።መንግሥትም መሰል ሰላማዊ አካሄዶችን እንደሚከተል በተደጋጋሚ ሲገልፅ ይሰማል።ከየትኛውም አካላት ጋር በጋራ ለመሥራት ዝግጁ እንደሆነ ይገልፃል።

በግጭት በጦርነት የሕዝብና የሀገር ፍላጎት አይሳካም።ምክክርና ውይይት ሰላምን ለማስፈን ሁነኛ አማራጮች ናቸው።ከመገዳደል ተቀምጦ መወያየት ይመረጣል።የጦር መሳሪያ አስቀምጦ እስክሪቢቶና ሃሳብ ይዞ በመወያየት ለሰላም፣ ለብልፅግና ምቹ የሆነች ሀገር እንድትሆን መሥራት ያስፈልጋል።

ምንም ነገር ያለ ሰላም ማሰብ ከባድ ነው።የሕዝብ ኑሮ መሻሻልም ሆነ የሀገር ምጣኔ ሀብት እድገት የሰላም መኖርና አለመኖር ጋር የተቆራኘ ነው።ሰላም እንዳይደፈርስ ግጭትም እንዳይኖር የቅድመ ዝግጅት ሥራ ይጠይቃል።ችግሮች ከተፈጠሩም በኋላ የከፋ ጉዳትና ቀውሶች ሳይኖሩ በውይይት፣ በቁርጠኝነት መፍታት የመንግሥትና የሌሎችንም ቁርጠኝነት ይጠይቃል።

ከግጭትና ጦርነት በፊት ስለሰላም ለውይይትና ምክክር እራስን ማስገዛት ካልተፈለገ ኪሳራ መውጫው ብቸኛ መንገድ ነው፤ ለዚህ ደግሞ ከአለፈ ታሪክ መማር አለብን።ለሚያጋጥሙ አለመግባባቶች በውይይት ፈጣን መፍትሔ መስጠት የሚያተርፈው ሁሉም ነው።የጋራ መግባባት የጋራ ተጠቃሚነትን ያመጣል።

ጦርነት መልከ ብዙ ዋጋ እንዳስከፈለን ለማንኛችንም የተሰወረ ትርክት አይደለም፤ ከከፈልናቸው አላስፈላጊ ዋጋዎች ተምረን ስለሰላም ደቀመዝሙር ልንሆን ይገባል።በጦርነት ዘላቂ ድል ማግኘት አይቻልም ፤ ለዘላቂ ሀገራዊ ሰላም ለሰላም ለተዘረጉ እጆች አዎንታዊ ምላሽ መስጠት ይጠበቅብናል።የትኛውም የሕዝባችን ጥያቄ ከሰላሙ አይበልጥም እና ስለ ሕዝባችን ሰላም ቀድመን ከራሳችን ሰላም ጋር እርቅ እናድርግ።

## ማስታወቂያ

አመልካች ገመቹ አበራ ዳባ _1996 G.C ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በAccounting ትምህርት ዘርፍ የተቀበልኩት ዲፕሎማ ጠፍቶብኛልና ምትክ ይሰጠኝ ብለዋል፡፡ ይህንን ሰነድ በሆነ አጋጣሚ በእጁ ያስገባ ሰው ካለ ማስታወቂያው በወጣ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሬጅስትራር ጽ/ቤት ይቅረብ፡፡ ካልሆነ ግን ምትክ የትምህርት ማስረጃ ለአመልካቹ የሚሰጥ መሆኑን ይገልጻል፡፡

**የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሬጅስትራር ጽ/ቤት**

## ማስታወቂያ

በከሳሽ ፌዴራል ዐ/ሕ እና በተከሳሽ ዮናስ ጎበና መካከል ስለአለው ኮንትሮባንድ ወንጀል ክስ ጉዳይ መነሻ ሆኖ ለተከሰሱበት ጉዳይ መልስ ለመስጠት ለ2/9/2016 ዓ.ም ከጠዋቱ 3፤00 ሰዓት ጌዴኦ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ችሎት እንዲቀርቡ ሆኖ የማይቀርቡ ከሆነ ጉዳዩ በሌለበት ታይቶ የሚወሰን መሆኑን እንድያውቁ ፍ/ቤቱ አዟል፤

**በደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግሥት ጌዴኦ ዞን**
**ከፍተኛ ፍ/ቤት የሬጅስትራል ሥራ ክፍል**

## ኦሮሚያ ክልል

የባለንብረቱ ስም ተማም ሱሌማን የተሽከርካሪው አይነት ሚኒባስ የሰሌዳ ቁጥር 03-80754 ኦሮ የሻንሲው ቁጥር JTF5522P70-0144595 ሞተር ቁጥር 2Db-AS10820 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው በ07/08/2016 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ ሊብሬውን ወድቆ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ ለጽ/ቤቱ ሪፖርት እንዲያደርጉ እያስታወቅን በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካላቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ የምንሰጥ መሆኑ እንገልፃለን፡፡

**በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት መስተዳደር ትራንስፖርት የሸገር ከተማ አስተዳደር**
**የገ/ጉጄ ክ/ከተማ ትራንስፖርት ጽ/ቤት**

## አዲስ አበባ አስተዳደር

የባለንብረት ስም አልፋ ፖወር ኤሌክትሪካል ቴክኖሎጂ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-A75675 የተሽከርካሪው አይነት ድርብ አገልግሎት የሻንሲ ቁጥር WDF4702311G016678 ሞዴል X-250D የሞተር ቁጥር 699301C0055506 የሊብሬ ቁጥር 116557 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪው ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ7/8/2016 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳውን ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ**
**ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን ቂርቆስ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ኡመር አሜን መሀመድ የሰሌዳ ቁጥር አአ 02-01-B47535 የተሸከርካሪው አይነት አውቶሞቢል የሻንሲ ቁጥር KSP90-2050362 ሞዴል DBA-KSP90-AHXNK የሞተር ቁጥር 1KR-0579279 የሊብሬ ቁጥር 116588 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር/ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው በ4/8/2016 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማስገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና**
**ቁጥጥር ባለሥልጣን ቂርቆስ ቅ/ጽ/ቤት**

በከሳሽ/አመልካች/የፍ/ባለመብት ቡና ኢንሹራንስ ኩባንያ አ.ማ እና በተከሳሽ/ተጠሪ/የፍ/ባለዕዳ አስፋው ታምራት መካከል ስላለው የፍትሐብሔር ክርክር ጉዳይ ከሳሽ ፍ/ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝ ተከሳሽ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ 6ኛ ባ/ኢ ችሎት እየታየ መሆኑን በዚህ ማስታወቂያ ጥሪ አውቀው መልሱን በፅሁፍ 10/08/2016 ዓ.ም በ3፡30 ሰዓት ይዘው ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**
**ንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ ችሎት**

በከሳሽ ፌ/ጠ/ዐ/ህግ እና በተከሳሾች 1. አቤል ኢሳያስ ተስፋዬ በሌላ ስሙ ቢኒያም ታደሰ ተሰማ፣ 2. ናትናኤል ረዳኢ ኪሮስ መካከል ስላለው ከባድ ውንብድና ወንጀል ክስ ጉዳይ ለ15/08/2016 ዓ.ም ሲሆን ቀነ ቀጠሮ በ3፡30 ሰዓት ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 2ኛ ግ/ከ/ው ወንጀል ችሎት እንዲቀርቡ የማይቀርቡ፣ ከሆነ ግን ክሱ በሌላችሁበት ታይቶ ውሳኔ የሚሰጥ መሆኑ አውቀው በእለቱ እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት**

በከሳሽ ፌ/ጠ/ዐ/ህግ እና በተከሳሾች 1ኛ አቶ ታዘባቸው ምህረቱ ጥጋቡ፣ 2ኛ ምስጋናው ንጉሴ በላይ መካከል ስላለው የጦር መሳሪያ ማዘዋወር ወንጀል ክስ ጉዳይ ለሚያዝያ 17 ቀን/2016 ዓ.ም ሲሆን ቀነ ቀጠሮ በ3፡45 ሰዓት ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 1ኛ ልዩ ልዩ ወንጀል ችሎት እንዲቀርቡ የማይቀርቡ፣ ከሆነ ግን ክሱ በሌላችሁበት ታይቶ ውሳኔ የሚሰጥ መሆኑ አውቀው በሰዓቱ እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት**

## የሐራጅ ማስታወቂያ

ስኬት ባንክ አ.ማ (የቀድሞ አዲስ የብድርና ቁጠባ ተቋም አ.ማ) ስማቸው ከዚህ በታች የተጠቀሱት ተበዳሪዎች የወሰዱትን ብድር ባለመክፈላቸው ባንኩ በአዋጅ ቁጥር 1147/2011 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ከዚህ በታች የተመለከቱት በመያዣነት ወይም በዋስትናነት የተያዙ ተሽከርካሪዎች ባሉበት ሁኔታ በግልጽ ሐራጅ አወዳድሮ ለመሸጥ ይፈልጋል፡፡

| ተ.ቁ | የተበዳሪው ስም | የዋስ ስም | ቅርንጫፍ | የሠሌዳ ቁጥር | የመኪናው ዓይነት | መነሻ ዋጋ | ሐራጁ የሚካሄድበት | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | ቀን | ሰዓት | |
| 1 | ይስሐቅ ዋርድያ | ይስሐቅ ዋርድያ | ልደታ | 01-35418 አ.አ | ግሎሪ | 1,000,000 | 24/08/2016 | ከጠዋቱ 4፡00 | ለመጀመሪያ ጊዜ |
| 2 | በቀሉ ዘውዴ | በቀሉ ዘውዴ | አራዳ | 02-09652 አ.አ | ሱዙኪ | 150,000 | 24/08/2016 | ከጠዋቱ 4፡00 | በድጋሚ |
| 3 | ሚካኤል ድንበሩ | አስቴር ተፈራ | ካዛንችስ | 02-72212 አ.አ | አቶዝ | 250,000 | 24/08/2016 | ከጠዋቱ 4፡00 | ለመጀመሪያ ጊዜ |
| 4 | ጫሊ መንገሻ | ጫሊ መንገሻ | ሰበታ | 03-B29230 አ.አ | ቶዮታ ፒክ አፕ | 1,600,000 | 24/08/2016 | ከጠዋቱ 4፡00 | ለመጀመሪያ ጊዜ |

**ማሳሰቢያ፡-**

1. ማንኛውም ተጫራች ወይም ሕጋዊ ወኪሉ የመኪናውን ሐራጅ መነሻ ዋጋ 1/4ኛውን በባንክ ክፍያ ማዘዣ /ሲፒኦ/ በባንኩ ስም በማሠራትና በማስያዝ መጫረት ይችላል፡፡
2. ሐራጁ የሚካሄደው ተሽከርካሪዎቹ በሚገኙበት ቦታ የሺደበሌ የባንኩ መጋዘን ግቢ ውስጥ ነው፡፡
3. ተራ ቁጥር 1፣ 2 እና 4 ላይ የተጠቀሱትን የተሽከርካሪዎች ሁኔታ ለማየት ተሽከርካሪዎቹ በሚገኙበት ቦታ የሺደበሌ የባንኩ መጋዘን ግቢ ውስጥ ከጨረታው ቀን ቀደም ብሎ ባሉት ቀናት ከሰኞ እስከ ዓርብ በሥራ ሰዓት በመገኘት ማየት ይቻላል፡፡
4. ተራ ቁጥር 3 ላይ የተጠቀሰውን ተሽከርካሪ ሁኔታ ለማየት ተሽከርካሪው በሚገኝበት ቦታ አቡነ ጴጥሮስ ሃውልት ፊት ለፊት በባንኩ የቀድሞ ቢሮ ግቢ ውስጥ ከጨረታው ቀን ቀደም ብሎ ባሉት ቀናት ከሰኞ እስከ ዓርብ በሥራ ሰዓት በመገኘት ማየት ይቻላል፡፡
5. ተራ ቁጥር 1 ላይ የተጠቀሰው ተሽከርካሪ ከ2016 ዓ.ም እስከ መጋቢት 2016 ዓ.ም ድረስ ብር 2,596.46 /ሁለት ሺህ አምስት መቶ ዘጠና ስድስት ብር ከ46/100/ ከመንግሥት የሚፈለግ ግብር አለበት፡፡
6. ተሽከርካሪዎቹ ከመንግሥት የሚፈለግ ግብር፣ ተጨማሪ እሴት ታክስ (VAT)፣ የቦሎ ክፍያ፣ የስም ማዛወሪያ እና ሌሎች ወጪዎችን የጨረታው አሸናፊ ይሸፍናል፡፡
7. በጨረታው ቀን የንብረቱ ባለቤት ወይም ሕጋዊ ወኪሉ በመገኘት ጨረታውን መከታተል ይችላሉ፤ ባይገኙም ጨረታው በሌሉበት ይካሄዳል፡፡
8. በጨረታው የተሻለ ዋጋ ያቀረበ ተጫራች ማሸነፉን የሚገልጽ ደብዳቤ ጨረታውን ካካሄደው የባንኩ የሕግ አገልግሎት ሲደርሰው ብቻ አሸናፊ ይሆናል፡፡
9. አሸናፊው ያሸነፈበትን ቀሪ ገንዘብ ጨረታውን ማሸነፉ በማስታወቂያ ሠሌዳ ከተለጠፈበት ቀን አንሥቶ በ15 ቀናት ውስጥ አጠቃሎ መክፈል ያለበት ሲሆን ካልከፈሉ ለሐራጅ መነሻ ያስያዘው ገንዘብ ተመላሽ አይደረግለትም፡፡
10. ባንኩ ጨረታውን በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**ለበለጠ መረጃ በስልክ ቁጥሮች፡- 011-1-26-22-33** ወይም 011-1-26-34-47 በመደወል ወይም በባንኩ ዋና መሥሪያ ቤት ሕግ አገልግሎት በግንባር በመቅረብ መጠየቅ ይቻላል፡፡

**ማስታወሻ**፡- ባንካችን ሐምሌ 5 ቀን 2015 ዓ.ም ከብሔራዊ ባንክ የሥራ ፈቃድ አግኝቶ ከሐምሌ 14 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ ቀድሞ አዲስ የብድርና ቁጠባ ተቋም አ.ማ የነበረውን የንግድ ምዝገባ ስያሜ ወደ ስኬት ባንክ አ.ማ የቀየረ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

## ስኬት ባንክ አ.ማ

ማህበራዊ

# ባለውለታዎቻችን

## የኢትዮጵያ ዘመናዊ ሙዚቃ እንቁ

**ክብረአብ በላቸው**

ገና የ13 ዓመት ታዳጊ ሳለ ሙዚቃን የጀመረው የቀድሞው ድምፃዊ ሙሉቀን መለሰ በ1958 ዓ.ም በፓትሪስ ሉሙምባ ምሽት ክለብ ፈጣን ኦርኬስትራን ተቀላቅሎ በመግባት ለሁለት ዓመታት ያህል መሥራት ችሏል። የሙዚቃ ድርሰት ሲመርጥ በጣም የተለየ ችሎታ እንዳለው ይነገርነታል።በዚህ ምክንያትም እንደ ዓለምፀሐይ ወዳጆ እና ተስፋዬ ለሜሳ ላሉ የሙዚቃ ደራሲያን ልዩ ቦታ ይሰጣል።

ተስፋዬ አበበ (ፋዘር)፣ ይልማ ገብረ አብ፣ አበበ መለሰ፣ ሰለሞን ተሰማ፣ ኩኩ ሰብስቤ እና ሌሎችም ግጥም እና ዜማ ቢሰጡትም፣ ግጥሞቹን እና ዜማዎቹን አንጥሮ የሚለይበት የራሱ ልዩ ተሰጥኦ አለው።በአንድ ወቅት በኢትዮጵያ ሬዲዮ እሁድ ጠዋት ፕሮግራም ላይ ባደረገው ቆይታ፣ "ለትዝታ ሙዚቃ ልዩ አመለካከት አለኝ፤ ፍቅር ውስጥም ትዝታ ስላለ ማለት ነው፤ እኔ ሙዚቃን ስሠራ በራሴ ቀለም ነው የምሠራው፤ ይህ ደግሞ ተወድዶልኛል፤ ባይወደድልኝ ኖሮ አድማጭ አላገኝም ነበር" ብሏል፡፡

እናቱ በልጅነቱ በመሞታቸው ምክንያት የሰው ፊት በማየቱ ይመስል "እናቴ ስትወልደኝ መች አማከረችኝ" የሚለው ዘፈኑ የተለየ ስሜት ይሰጣል። ሙሉቀን መለሰ በቀድሞው ጎጃም ጠቅላይ ግዛት አነደድ ወረዳ ዳማ ኪዳነ ምሕረት በምትባል መንደር በ1946 ዓ.ም ነው የተወለደው። አስር ዓመት ሲሆነው እናቱ ስለሞቱ አዲስ አበባ ይኖሩ የነበሩት አጎቱ እንዲማር ብለው የወሰዱት ሲሆን፣ ኮልፌ ጳውሎስ ትምህርት ቤት ገብቶ መማር ጀመረ።

በዚህ መሀል የአጎቱ ቤት ስላልተመቸው ከቤት ወጥቶ ኮልፌ ሕፃናት ማሳደጊያ ገባ። የተቋሙ አስተዳዳሪ ይወዱት ስለነበር 'ኤልቪስ' ይሉት እንደነበረ ከስብሐት ገ/እግዚአብሔር ጋር በ1973 ዓ.ም 'ፀደይ መጽሔት' ላይ ባደረገው ቃለመጠይቅ ላይ ተናግሯል። ለሙዚቃ ልዩ ፍቅር ስለነበረው ከትምህርቱ ጎን ለጎን በልጆች ማሳደጊያው አካባቢ በተከፈተው የሙዚቃ ትምህርት ቤት ገብቶ ለስድስት ወራት ሰልጥኗል። በዚህ መሀል እህቱ ስለታመመች ወደ ሀገር ቤት ሄደ። ጥቂት ቆይቶም ወደ አዲስ አበባ ተመልሶ ሥራ ማፈላለግ ጀመረ።

ወደ ምድር ጦር ሙዚቃ ክፍል ሄዶ በሙዚቀኛነት ሊቀጠር ቢጠይቅም ተቀባይነት ሳያገኝ ቀረ።ነገር ግን ልጅነቱን እና ችግሩን አይተው ሻይ የማፍላት ሥራ ሰጡት። በዚህ ሥራ ላይ እያለም የተከሰተውን ሲያስታውስ፣ "ምድጃዋ የኤሌክትሪክ ነበረች፤ ባንድ ቀን ውስጥ ሶስት ጊዜ ኮረንቲ ያዘኝ" ብሎ ነበር። በዚህ ሁኔታ ለስድስት ወር ያህል ከሠራ በኋላ ሥራውን ትቶ በመውጣቱ ለተወሰኑ ወራት ተንከራተተ።

ከብዙ መንከራተት በኋላ አቡነ ጴጥሮስ ሐውልት አካባቢ በሚገኝ አንድ ሻይ ቤት ተቀጥሮ መሥራት ጀመረ። ሙሉ ቀን ታታሪ እና አመለ ሸጋ በመሆኑ የሻይ ቤቱ ባለቤት ይወዱት እና ይረዱት ነበር። በሻይ ቤቱ እየሠራ በነበረበት ወቅት ሀርሞኒካ የሚጫወት ጓደኛ ስለነበረው ሻይ ቤቱ ቁጭ ይሉና ጓደኛው ሀርሞኒካውን ሲጫወት ሙሉቀን ይዘፍናል።

አንድ ቀን ሙሉቀን እና ጓደኞቹ አብረው ሲጫወቱ ያመሹና አንዱን ጓደኛቸውን ለመሸኘት ሲሄዱ፣ ደጃች ውቤ ሰፈር ሲደርሱ የውቤ በረሃ የምሽት ቤቶች ልዩ ልዩ ቀለማት መብራቶች ሙሉቀንን በጣም ያስደንቁታል። በተለይም ትኩረቱን ስለሳበው አንድ ለየት ያለ ቤት ጓደኞቹን ሲጠይቃቸው ቤቱ 'ፓትሪስ ሉሙምባ የምሽት ክለብ ይባላል' ይሉታል።

ወደ ክለቡ ገብቶ ሥራ እንዲሰጡት የክለቡን ባለቤት ወ/ሮ አሰገደች አላምረውን ጠየቃቸው። ሙዚቃ እንዲፈተን ከቻለ እንደሚቀጥሩት፣ ካልቻለ ደግሞ ሌላ ሥራ እንደሚሰጡት ቃል ገቡለት። ጥላሁን ገሠሠ እና ዓለማየሁ እሸቴን አስመስሎ ይዘፍን የነበረው ሙሉቀን የተሰጠውን ዕድል ተጠቅሞ በባዶ እግሩና በቁምጣ ሱሪ መድረኩ ላይ ወጥቶ "ለእውነት እሞታለሁ አልሳሳም ለነፍሴ" እና "እንክርዳድ" የተሰኙ የጥላሁን ዘፈኖችን አቀረበ።

እዚያው ምግብ እና ማደሪያ ተሰጥቶት በ90 ብር ወርሃዊ ደመወዝ መሥራት ጀመረ።ወቅቱን ሲያስታውስም፣ "ዘጠና ብር ስቀጥር ሚሊየነር የሆንኩ ነው የመሰለኝ!" ብሎ ነበር።



**ሙሉቀን መለሰ**

በፓትሪስ ሉሙምባ የምሽት ክለብ እየተጫወተ እያለ ፖሊስ ኦርኬስትራ ተቀጠረ።ለፖሊስ ኦርኬስትራ በተቀጠረ በሦስተኛ ቀኑ ከኦርኬስትራው ጋር ወደ መቀሌ ተጉዞ የ"ወይዘሪት ትግራይ" የቁንጅና ውድድር ሲደረግ የጥላሁን ገሰሰን ዘፈኖች ዘፈነ። ታዳሚውም ሙዚቃውን በጣም ወደደው፡፡

ተስፋዬ አበበ(ፋዘር) የደረሷቸውን "እምቧይ ሎሚ መስሎ"፣ "እናቴ ስትወልደኝ መች አማከረችኝ" እና "ልጅነት" የተባሉትን ሦስት ዘፈኖች በሕዝብ ፊት ይዘፍን ጀመር። በወቅቱ የኦርኬስትራው ድርሰት እና ዝግጅት ኃላፊ የነበሩት ተስፋዬ አበበ (ፋዘር) ሙሉቀን ወደ ፖሊስ ኦርኬስትራ የተቀላቀለበትን ሁኔታ ሲያስታውሱ፣ "በምሽት ክለብ ብዙ ቢቆይ ኖሮ ከዕድሜው አንጻር ይበላሽ ነበር፤ እኛ ጋር እንደመጣ ምንም ልምምድ ሳያስፈልገው ነበር ሥራ ውስጥ የገባው" ይላሉ።በፖሊስ ኦርኬስትራ ውስጥ በሠራቸው ዘፈኖች ታዋቂነቱ እየጨመረ ሄደ። ጋዜጦችም "ኮከብ ድምጻዊ ተጫዋች" በማለት ስለሱ መጻፍ ጀመሩ። ከሦስት ዓመታት በኋላ ከፖሊስ ኦርኬስትራ ጋር ተለያየ።

ሰሎሞን ተሰማ የደረሰውን 'የዘላለም እንቅልፍ' የሚለውን ግጥም እና አቡበከር አሸኬ የደረሰውን 'ያላየነው የለም' የሚሉ ዘፈኖችን በሸክላ አስቀርጾ ለሕዝብ ለቀቃቸው። በዚህም ታዋቂነቱ እየጨመረ መጣ። በ1972 ዓ.ም ላይ ደግሞ ከዳህላክ ባንድ ጋር ተቀላቅሎ ሠርቷል። እስከ 1980ዎቹ ድረስ በነበሩት ዓመታት እጅግ ተወዳጅ የሙዚቃ ሥራዎችንም ሠርቷል። ሙሉቀን በተጨማሪም ከእኩዬተርስ ባንድ እና ከኢትዮ ስታር ባንድ ጋር የሙዚቃ ሥራዎቹን ሠርቷል፡፡

ሙዚቃ በቃኝ ብሎ ራሱን ከሙዚቃው ዓለም እስካገለለበት ጊዜ ድረስ ለ17 ዓመታት በርካታ የሙዚቃ ሥራዎችን ለትውልድ አበርክቷል። በተለይ ባሕላዊ ጨዋታዎችን በዘመናዊ ለዛ ሲጫወት ወደር የለሽ ነበር። ገጣሚ እና ደራሲው ይልማ ገብረ አብ እንደሚለው እንደ ሳንሱር ሙሉቀንን ያማረረው ነገር የለም።በሳንሱር ስድስት ሥራዎቹ ሲሰረዙበት እንባ አውጥቶ ማልቀሱን ከአበበ መለሰ ጋር እንደተመለከቱት ይልማ ያስታውሳል፡፡

ሙዚቃን አቁሞ ወደ መንፈሳዊ መዝሙር የሄደበት የመጨረሻ ሙዚቃው "ነይ ነይ ወዳጄ ነይ ነይ" የሚለው ዘፈን እንደሆነ የትራምፔት ተጫዋቹ እና ሙዚቃ አቀናባሪው ሻምበል መኮንን መርሻ ያስታውሳሉ።ከ1980ዎቹ በኋላ ፊቱን ወደ መንፈሳዊ ሥራዎች በማዞር የመዝሙር ሥራዎችን እየሠራ እስከ ህልፈተ ሕይወቱ ድረስ በሀገረ አሜሪካ ኑሮውን አድርጎ ቆይቷል።

ተስፋዬ አበበ(ፋዘር) የደረሷቸውን "እምቧይ ሎሚ መስሎ"፣ "እናቴ ስትወልደኝ መች አማከረችኝ" እና "ልጅነት" የተባሉትን ሦስት ዘፈኖች ውስጥ እናቴ ስትወልደኝ መች አማከረችኝ" ያለው ሰንኝ እንዲህ ይላል...

የለም ህያውነት ዘላለም መደሰት<br>
ከሞት ተከልሎ እንዳማሩ መቅረት<br>
የዓለም አሻጋሪ ኃላፊ ሲነጋ<br>
ሳያውቀው ይሸኛል በተኛበት አልጋ።

ሌላዋ ከፍተኛ ዝና የተጎናፀፈባት ዘፈኑ "ሄደች አሉ" በ1964 ዓ.ም. በሸክላ ተቀርጾ ስወጣ፣ ከሦስት ዓመታት በኋላ "ወተቴ ማሬ" እና "እቴ እንዴት ነሽ ገዳዎ" የተሰኙት ዜማዎቹ በተመሳሳይ በሸክላ ታትመው አድማጭ ጆሮ ደረሱ። ሙሉቀን ለየት ያለ አጨዋወቱ ከፍተኛ ተወዳጅነትን አትርፎለታል። ሙሉቀን መለሰ ባሕላዊ እና ዘመናዊ ስልቶችን አዋህዶ በመጫወትም ይታወቃል።

<<ስትሞት ስምህ ህያው ሆኖ ከመቃብር በላይ እንዲኖር ከፈለክ ወይ መጽሐፍ ፃፍ አልያም የማይረሳ ታሪክ ሥራ እንደሚባለው>> ሙሉቀን መለሰ በኢትዮጵያ የሙዚቃ ታሪክ በሥራዎቹ የማይሞት ህያው ስም ያለው የማይዘነጋ የኢትዮጵያ ዘመናዊ ሙዚቃ ባለታሪክ ነው።

በአንድ ወቅት ከሙዚቃ ሥራዎቹ መካከል የትኛውን አብልጦ እንደሚወድ የተጠየቀው ሙሉቀን ሁሉንም ሥራዎቹን ዕኩል እንደሚያያቸው በመግለጽ በዜማ እና በዘፈን የተለዩ ናቸው የሚላቸውን ጠቅሶ ነበር።

"...በጣም የሚያረኩኝ...በዜማው እና በዘፈኑ... 'ሰውነቷ' እና 'ሆዴ ነው ጠላትሽ'...በሙዚቃ ጥራት እና ባሠራር ደግሞ፣ ሙላቱ አስታጥቄ ያቀነባበራቸው እና ከዳህላክ ባንድ ጋር የዘፈንኳቸው 'ቼ በለው' እና 'ውቢት" የተባሉትን ለእሱ ከሌሎቹ የተለዩ ነበር።

ሙሉቀን እንደ በርካታ የኢትዮጵያ ዘመናዊ ሙዚቀኞች ሁሉ ወደ ሙዚቃው ዓለም የተሳበው ድምጻዊ

**ሙሉቀን እንደ በርካታ የኢትዮጵያ ዘመናዊ ሙዚቀኞች ሁሉ ወደ ሙዚቃው ዓለም የተሳበው ድምጻዊ ጥላሁን ገሰሰን አይቶ መሆኑን እና ለረዥም ጊዜ እርሱን እያስመሰለ ሲሠራ መቆየቱን ይናገራል**

ጥላሁን ገሰሰን አይቶ መሆኑን እና ለረዥም ጊዜ እርሱን እያስመሰለ ሲሠራ መቆየቱን ይናገራል። ሙሉ ለሙሉ በሙዚቃ ሥራ ውስጥ መሳተፍ ከጀመረበት ከፓትሪስ ሉሙምባ በኋላ በተለያዩ የአዲስ አበባ የምሽት ክበቦች ሲሠራ ቆይቷል።

ሙሉቀን 17 ዓመታትን ያህል በሙዚቃው ሕይወት ውስጥ ሲቆይ ከድምጻውያን በቅድሚያ የዓለማየሁ እሸቴ እና የምኒልክ ወስናቸው አድናቂ መሆኑን በአንድ ቃለመጠይቁ ላይ ተናግሮ ነበር። ከእነርሱ ባሻገር የብዙነሽ በቀለ፣ የሒሩት በቀለ፣ የመሐሙድ አህመድ፣ የጥላሁን ገሰሰ አድናቂም መሆኑን ይናገራል።

ከ17 ዓመታት የድምጻዊነት ሕይወት በኋላ ሙሉቀን ዘፈንን ያቆመው ወደ መንፈሳዊ ሕይወት በማተኮሩ ነበር። ሙሉቀን ለመጨረሻ ጊዜ የተጫወተው ሙዚቃ 'ነይ ነይ ወዳጄ' የተሰኘውን መሆኑን የሙያ ባልደረቦቹ በአንድ ወቅት በሰጡት ቃለ ምልልስ ላይ ተናግረው ነበር። ከሀገር ወጥቶ ኑሮውን በአሜሪካ ካደረገ አራት አስርት ዓመታትን አስቆጥሯል፡፡

ሙሉቀን ከዓለማዊው የሙዚቃ ሕይወት በመውጣት መንፈሳዊነትን አጥብቆ ኑሮውን በአሜሪካ አሌክሳንደሪያ ቨርጂኒያ ውስጥ ካደረገ በኋላ ወደ ሀገሩ ተመልሶ አያውቀም። በእነዚህ ዓመታት ሙሉቀን መለሰ ከዘፈን ሕይወት ራሱን ካገለለ በኋላ ፊቱን ወደ መንፈሳዊ ዝማሬ አዞረ። በዚህም የተለያዩ የመዝሙር ሥራዎችን ለወንጌል አማኞች አቅርቧል።

ምንም እንኳን ሙሉቀን መለሰ ሙዚቃን ከቆመ አርባ ዓመታት ሊሆነው የተቃረበ ቢሆንም ከዓመታት በፊት የሠራቸው ሙዚቃዎቹ ዘመናትን በመሻገር አሁን ድረስ በተለያዩ ትውልዶች ተወዳጅ እና የሚደመጡ ናቸው። ከዚህም የተነሳ በሸክላ እና በካሴት ዘመን የተጫወታቸው ሙዚቃዎቹ እሱ መዚቃን ካቆመ በኋላ በተፈጠሩት ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች ተቀናብረው በሲዲ እና በኢንተርኔት የሙዚቃ ማድመጫዎች በኩል እየተደመጡ ይገኛሉ።

በተጨማሪም የሙሉቀን ሙዚቃዎች በትውልዶች መካከል ካገኙት ተወዳጅነት የተነሳ በተለያዩ ጊዜያት ጥቂት የማይባሉ ወጣት ድምጻውያን ደግመው ተጫውተዋቸው ለአድማጮች መቅረባቸው ይታወቃል።

በአጎቱ ስም የሚጠራው ሙሉቀን መለሰ፣ የተወለደው ከአቶ ታምር ጥሩነህ መሆኑን በአንድ ወቅት ሲናገር "ይህንን ስም ሳልቀይር መቅረቴ ይቆጨኛል" ብሎ ነበር። ሙሉቀን ከእናቱ ሞት በኋላ ሊያሳድጉ ወደ አዲስ አበባ ያመጡት አጎቱ አቶ መለሰ፣ በመማሪያ ደብተሩ ላይ ሙሉቀን መለሰ ብለው ከጻፉ በኋላ ነበር በአጎቱ ስም እየተጠራ የቀጠለው።

ከምንም ተነስቶ ኮከብ ለመሆን የበቃው የቀድሞው ድምጻዊ ሙሉቀን መለሰ በተወለደ በ70 ዓመቱ ማክሰኞ ሚያዚያ 1 ቀን 2016 ህልፈተ ሕይወቱ በአሜሪካን ሀገር ተሰምቷል።እሱ በአካል ቢያልፍም በሥራዎቹ ግን ህያው ሆኖ ከአድናቂዎቹ ጋር ይኖራል።እኛም ተወዳጁን ሙዚቀኛ ነፍስ ይማር እያልን፤ ለቤተሰቦቹና ወዳጅ ዘመዶቹ መፅናናትን እንመኛለን።